**የኢትዮጵያ የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕግ**
**አዋጅ ቁጥር.../2011**

ኢትዮጵያዊያን በማንኛውም ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግባቸው በቀጥታ እና በነፃነት በመረጧቸው ተወካዮች አማካይነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣናቸውን በተግባር ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየደረጃው በሚደረጉ ሁሉን አቀፍ ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫዎች በእኩልነትና በነጻነት በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ ፍቃዱን በመግለጽ የመሳተፍ መብቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማንኛውም የምርጫ እንቅስቃሴ ዓለም አቀፍ የምርጫ መርሆዎችን አካትቶ በያዘ ህግ እንዲመራ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች የተለያየ ዓላማና አመለካከታቸውን በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ ለመራጩ ሕዝብ በመግለጽ የሚሳተፉበት፥ መራጩ ሕዝብም በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃነት በመግለፅ ወኪሎቹን የሚመርጥበት የምርጫ ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ዜጎች በሚመሠርቱት ወይም በአባልነት በሚቀላቀሉት የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የሚኖራቸውን መብትና ግዴታ፥ እንዲሁም ፓርቲው ሕጋዊ ሰውነት የሚያገኝበትን ሁኔታ እና በድርጅትነት ሲንቀሳቀስ መከተልና ማክበር ያለበትን መሠረታዊ መርሆች መደንገግ በማስፈለጉ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች በመዋሀድ ፣ ግንባር በመፍጠር ወይም በመቀናጀት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለፍትሃዊ፣ ሰላማዊ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሥርአት መስፈን በምርጫ የሚሣተፉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የግል ዕጩዎች ገንቢ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ግልፅ አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ምርጫዎች በመልካም ሥነ ምግባር የሚመሩ ነጻ፣ ፍትሃዊ ፣ሰላማዊ፣ ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆኑና እንዲሁም በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን እንዲያገኙ ለማድረግ በምርጫ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች የሚመሩባቸውን የሥነ ምግባር መርሆች መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምርጫ ሂደት ለሚነሱ አለመግባባቶች አስተዳደራዊ እና የዳኝነት መፍትሔ የሚሰጡ ተቋማትን እና አሰራራቸውን መወሰን በማስፈለጉ፤

በገለልተኝነት ምርጫን እንዲያስፈጽም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 መልሶ መቋቋሙን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕግ አዋጅ ቁጥር ...." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፤

1. "ኢ.ፌ.ዴ.ሪ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ነው፡፡

2. "ህገ መንግስት" ማለት የኢ.ፌ.ዴ. ሪ ህገመንግስት ነው፡፡

3. "ክልል" ማለት በህገመንግስቱ አንቀፅ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል አዲስ አበባን እና ድሬዳዋን ይጨምራል፡፡

4 "ቦርድ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 መልሶ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡

5. "ምርጫ" ማለት በፌዴራልና በክልል ህገ መንግስታት እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት የሚካሄድ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያ ወይም የድጋሚ ምርጫ ነው፡፡

6. "ጠቅላላ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

7. "የአካባቢ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የማዘጋጃ ቤት፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

8. "ማሟያ ምርጫ" ማለት በመራጮች ውሳኔ መነሳትን ጨምሮ በማንኛውም ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ የተጓደሉ የምክር ቤት አባላት መቀመጫዎችን ለመሙላት የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡

9. "ድጋሚ ምርጫ" ማለት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀፅ 7(16) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቦርዱ የምርጫ ውጤቱ እንዲሰረዝ ሲወስን፤ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 154 መሰረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን፤ ወይም

እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡

10. “ህዝበ ውሳኔ” ማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት ወይም በሌላ ህግ መሠረት ሲወሰን የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት ወይም የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ የሚደረግ የድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት ነው፡፡

11. “የመራጮች መዝገብ” ማለት በየደረጃው ለሚካሄድ ምርጫ መራጩ ህዝብ በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት የሚመዘገብበት መዝገብ ነው፡፡

12. “የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ማለት አንድ ሰው በመራጭነት ሲመዘገብ ከመዘገበው የምርጫ ጣቢያ የሚሰጠው የመራጭነት ማረጋገጫ ነው፡፡

13. “የፖለቲካ ፓርቲ” ወይም “የፖለቲካ ድርጅት” ማለት ዜጎች ተደራጅተው የሚመሠርቱት የፖለቲካ ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ፣ በክልል ወይም ከክልል በታች ባለ ደረጃ በምርጫ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በዚህ አዋጅ መሠረት ተመስርቶ የሚንቀሳቀስ ተቋም ነው፡፡

14. “የፖለቲካ ፓርቲ ሃላፊዎች” ማለት እንደሁኔታው የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ የሥራ አስፈጻሚ አባላት፣ ወይም በተመሳሳይ የሥልጣን ደረጃ ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ናቸው፣

15. “የምርጫ ክልል” ማለት ለምርጫ አፈፃፀም እንዲያመች እና ህዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በህግ መሠረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው፡፡

16. “የምርጫ ጣቢያ” ማለት በየደረጃው ለሚካሄዱ ምርጫዎች የመራጭ ምዝገባ የሚካሄድበት፣ መራጮች ድምፅ የሚሰጡበት እና የድምጽ ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፡፡

17. “የምርጫ አስፈፃሚ” ማለት ቦርዱን ጨምሮ በየደረጃው ምርጫን ለማስፈፀም የሚመደብ ሰው ነው፤

18. “እጩ ተወዳዳሪ” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በግሉ የተመዘገበ ሰው [ግለሰብ] ነው፤

19. “ታዛቢ” ማለት የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢና የውጭ የምርጫ ታዛቢዎችን ያካትታል፡፡

20. “የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ” ማለት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ከቦርዱ ፈቃድ አግኝቶ በወኪሉ አማካይነት ምርጫን የሚታዘብ በህግ የተመዘገበ፣ ገለልተኛና ለትርፍ ያልተቋቋመ፥ መንግሥታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡

21. “የውጭ የምርጫ ታዛቢ” ማለት አገሪቱ በተቀበለቻቸው ስምምነቶች መሠረት፤ በመንግስት ምርጫን እንዲታዘቡ የሚጋበዙ መንግስታት ወይም ዓለምአቀፍ፣ አህጉራዊ፣ ክፍለ አህጉራዊ ተቋማት እንዲሁም በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው፡፡

22. “ተቀማጭ ወኪል” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ተወክሎ በምርጫ ክልልና በምርጫ ጣቢያ በመቀመጥ የምርጫ ሂደቱንና የወካዩን መብት መከበር የሚከታተል ሰው ነው፡፡

23. “ተንቀሳቃሽ ወኪል” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግል እጩ ተወክሎ በአንድ ምርጫ ክልል ውስጥ በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች እየተንቀሳቀሰ የምርጫ ሂደትንና የወካዩን መብት መከበር የሚከታተል ሰው ነው፡፡

24. “ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ " ማለት በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፣ በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ ለሚነሱ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ በዚህ አዋጅ መሠረት ለምርጫ ወቅት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡

25. “ውህደት” ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ በህግ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ሕጋዊ ሰውነታቸውን በመተው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ የሚመሰርቱበት ሂደት ነው፣

26. “ግንባር” ማለት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ሕጋዊ ህልውናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ የሆነ ስያሜ፣ የፖለቲካ ፕሮግራም እና መተዳደሪያ ደንብ ይዘው ለመንቀሳቀስ ሲወስኑ የሚመሠርቱት ድርጅት ነው፣

27. “መቀናጀት” ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ሕጋዊ ሰውነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ወቅት/ምርጫውን ለማሸነፍ ወይም ለሌላ መሰል ጊዜያዊ አላማ በጋራ ለመሥራት ተስማምተው የመቀናጀት የምስክር ወረቀት የሚያገኙበት ሁኔታ ነው፣

28. “መተካት” ማለት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ነባር ስሙንና ፕሮግራሙን በመቀየር አዲስ ስምና ፕሮግራም በማዘጋጀት በዚሁ ስሙ እና ፕሮግራሙ እንዲታወቅ አስፈላጊውን መረጃ ለቦርዱ በማቅረብ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመዘገብበትና የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ነው፣

29. “ሰው” ማለት ሕጋዊ ወይም የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

30. በዚህ አዋጅ ውስጥ ማንኛዉምበወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ፡-

1/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረግ ጠቅላላ ምርጫ እንዲሁም እንደአግባብነቱ የአካባቢ ምርጫ፣ የማሟያ ምርጫ፣ የድጋሚ ምርጫ እና በህገመንግስቱ መሠረት በሚካሄድ ህዝበ ውሳኔ ላይ፤ እንዲሁም

2/ የፖለቲካ ፓርቲ ለሚመሠርቱ ዜጎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና ኃላፊዎች፣ አባላት ፥ወኪሎች እና ተጠሪዎች፣ የፓርቲና የግል እጩ ተወዳዳሪዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር ወይም ውህደት ላይ፣ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለምርጫ እና አስፈጻሚ አካላት
## ምዕራፍ አንድ
## የምርጫ ሥርአት፣ መርሆች እና አይነቶች

### 4. የምርጫ ሥርዓት

1. በፌዴራል ህገ መንግስት መሠረት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለሚደረግ ምርጫ በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሚወዳደሩት ዕጩዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘው አሸናፊ ይሆናል፡፡ በክልል ህገ መንግስታት መሠረት ለክልል ምክር ቤቶች የሚመረጡት ተወካዮች ከአንድ በላይ ሲሆኑ ከተወዳዳሪዎቹ መካከል በቅደም ተከተል አብላጫ ድምጽ ያገኙ ዕጩዎች አሸናፊ ይሆናሉ፡፡

2. የክልል ምክር ቤት አባላት ምርጫን የሚመለከቱ የክልል ህጎች በህገ መንግስቱና በዚህ አዋጅ ከተቀመጡ ምርጫን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

### 5. የምርጫ መርሆዎች

1. ማንኛውም ምርጫ ሁሉ አቀፍ፣ ቀጥተኛ፣ በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበት እና ያለ ምንም ልዩነት በሚደረግ ህዝባዊ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

2. የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተገደበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መምረጥ ወይም መመረጥ ይችላል፤ ሆኖም ለመምረጥም ሆነ ለመመረጥ አይገደድም፡፡

3. እያንዳንዱ መራጭ የሚሰጠው ድምፅ እኩል ነው፡፡

4. እያንዳንዱ መራጭ ድምጽ መስጠት የሚችለው በአካል በመገኘት ነው፡፡

## 6. የምርጫ አይነቶች

በኢትዮጵያ የሚካሄዱ ምርጫዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ጠቅላላ ምርጫ፣
2. የአካባቢ ምርጫ፣
3. ማሟያ ምርጫ፣
4. ድጋሚ ምርጫ፣
5. ህዝበ ውሳኔ፣

## 7. ጠቅላላ ምርጫ

1. ጠቅላላ ምርጫ በየአምስት ዓመቱ የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

2. ጠቅላላ ምርጫ በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና ጉዳዩ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሲያገኝ በተለያየ ጊዜ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3. ለፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአንድ የምርጫ ክልል አንድ ተወካይ ብቻ ይመረጣል፡፡

4. የክልል ምክር ቤቶች አባላት ቁጥር በየክልሉ ህግ መሠረት የሚወሰን ሆኖ ከአንድ የምርጫ ክልል ከአንድ ተወካይ በላይ ለክልል ምክር ቤቶች አባልነት ሊመረጥ ይችላል፡፡ክልሎች የምክር ቤቶቻቸውን አባላት ቁጥር ለመቀየር የሚሰጡት ውሳኔ ከእጩዎች የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ስድስት ወር አስቀድሞ መሆን ይኖርበታል፡፡

5. በህገ መንግስቱ አንቀጽ 61 (3) መሠረት አንድ የክልል ምክር ቤት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት በቀጥታ በህዝብ እንዲመረጡ ሲወስን ምርጫው ከጠቅላላ ምርጫ ጋር አንድ ላይ የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ይህ ሲሆን የክልል ምክር ቤቱ ቀጣዩ ምርጫ ከመደረጉ ስድስት ወራት አስቀድሞ ውሳኔውን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 8. የአካባቢ ምርጫ

1. የአካባቢ ምርጫ በህግ በተደነገገው መሠረት በየደረጃው የሚካሄድ የዞን፣የወረዳ፣ የከተማ፣ የማዘጋጃ ቤት፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

2. የአካባቢ ምርጫ የሚካሄድበት ጊዜና ከአንድ ምርጫ ክልል በየደረጃው ለምክር ቤቶቹ የሚመረጡት ተወካዮች ቁጥር እያንዳንዱ ክልል በሚያወጣው ሕግ ይወሰናል፡፡

3. በንኡስ ቁጥር 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ህገ መንግስት አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀጽ 2(መ) እና አንቀፅ 55 (15) መሠረት የአካባቢ ምርጫዎችን በተመለከተ ሁሉም ሊያደርጋቸው የሚገቡ መስኪያዎችን የሚያስቀምጥ ህግ ሊያወጣ ይችላል፡፡

4. የአካባቢ ምርጫን የሚመለከቱ የክልል ህጎች በህገ መንግስቱ እና በዚህ አዋጅ ከተቀመጡ ምርጫን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

5 በዚህ አዋጅ ለጠቅላላ ምርጫ የተደነገገው እንደ አግባብነቱ በአካባቢ ምርጫ ላይም የሚፈጸም ሆኖ ቦርዱ በየደረጃው የምርጫ ክልሎች ወይም ጣቢያዎች አደረጃጀት፤ የምርጫ አስፈጻሚዎችና ታዛቢዎች አመዳደብ፤ የመራጭ እና የእጩዎችን ምዝገባ ቦታና ሂደት፤ የግል እጩ ተወዳዳሪዎች የድጋፍ ፊርማ ብዛት እና ሌሎች ጉዳዮችን ይህን አዋጅ መሠረት በማድረግ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

## 9. የማሟያ ምርጫ

1. የማሟያ ምርጫ የሚካሄደው፡-

   ሀ. በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች በተለያየ ምክንያት የተጓደሉባቸው አባላት እንዲሟሉላቸው ለቦርዱ ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ ወይም

   ለ. ተፈጻሚነት ባለው ህግ መሠረት የቀረበ የይውረድልን ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ ነው፡፡

2. ቦርዱ ጥያቄው በደረሰው በስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የማሟያ ምርጫ ያካሂዳል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ምክር ቤት የሥራ ዘመኑ ሊጠናቀቅ የቀረው ጊዜ ስድስት ወርና ከዚያ በታች ከሆነ የማሟያ ምርጫ አይካሄድም፡፡

## 10. ድጋሚ ምርጫ

1. **ድጋሚ ምርጫ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊካሄድ ይችላል፤**

   **ሀ.** በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀፅ 7(16) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቦርዱ የምርጫ ውጤት እንዲሰረዝና ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን፥ በውሳኔው ላይ በዚህ አዋጅ አንቀጽ_መሰረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቦም እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የቦርዱን ውሳኔ በማጽናት የምርጫ ውጤቱ ተሰርዞ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን፤

   ለ. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 61(3) መሠረት እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት ያልተቻለ እንደሆነ፡፡

2. **ድጋሚ ምርጫ ሲካሄድ፤**

ሀ. ሌላ አዲስ የመራጮች ምዝገባ ሳያስፈልግ በምርጫ ክልሉ ወይም ችግሩ በተከሰተባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ተመዝግበው በነበሩ መራጮች እንደገና ይካሄዳል፡፡

ለ. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) መሠረት ምርጫ እንዲካሄድ ሲወሰን አዲስ የእጩዎች ምዝገባ ሳያስፈልግ ቀድሞ በተመዘገቡ እጩዎች መካከል ብቻ ይደረጋል፡፡

ሐ. ለድጋሚ ምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

የድጋሚ ምርጫ ዝርዝር አፈፃፀም ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

**11. ህዝበ ውሳኔ**

1. ቦርዱ በህገ መንግስቱ ወይም በሌሎች ህጎች መሠረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የህዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምጽ እንዲሰጥ ህዝበ ውሳኔ የሚሰጥበት ምርጫ ያዘጋጃል፡፡
2. ህዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ የወሰነው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ቦርዱ ህዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ህዝበ ውሳኔውን ያከናውናል፡፡
3. ቦርዱ በህገ መንግስቱ ስልጣን ከተሰጠው አካል ጋር በመመካከር ድምጽ የሚሰጥበትን ቀን፥ በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ የሚሠፍረው ለውሳኔ የቀረበው አማራጭ አጻጻፍ እና የህዝበ ውሳኔውን አስመልክተው የሚደረጉ የቅስቀሳ ዓይነቶችን ይዘት ይወስናል፡፡
4. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>
## <u>የምርጫ ማስፈጸሚያ አደረጃጀቶች</u>

**12. ጠቅላላ**

በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀፅ 7 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ቦርዱ፣

1. ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በሁሉም ክልሎችና ከዚያ በታች ባሉ የአስተዳደር እርከኖች ያደራጃል፡፡ እንደየክልሉ ሁኔታ በዞን ወይም በምርጫ ክልል እርከን የሚቋቋሙ ጽህፈት ቤቶች የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣሉ፣ በእያንዳንዱ ጽሕፈት ቤት ውስጥ የሚቀመጥ ቋሚ የመራጮች መዝገብ ያደራጃሉ፤ በየጊዜው እያስተካከሉ የመረጃውን ወቅታዊነት እንዲጠበቅ ያደርጋሉ፡፡ የምርጫ ክልሎችን ለመወሰን ለሚደረጉ ጥናቶች ድጋፍ ይሰጣሉ፤ ሌሎች ለምርጫ የሚያስፈልጉ ዝግጅቶችና የማስተባበር ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2. የምርጫ ክልሎችና የምርጫ ጣቢያዎችን በመላ አገሪቱ ያቋቁማል፡፡

## 13. የምርጫ ክልሎች ስለማቋቋም

1. ለጠቅላላ ምርጫ አፈፃፀም የሚያገለግሉ የምርጫ ክልሎች እንደሚከተለው ይደራጃሉ፡፡

   ሀ. ለምርጫ አፈፃፀም ዓላማ የክልል መንግሥታት ድንበር እንደተጠበቀ ሆኖ አገሪቱ የወረዳ አስተዳደርን መሠረት በማድረግ የሚከፋፈሉ፥ በህዝብ ቆጠራ ውጤት መሠረት ማስተካከያ ሊደረግባቸው በሚችሉ ቋሚ የምርጫ ክልሎች ትከፋፈላለች፣

   ለ. አገሪቱ እያንዳንዳቸው አንድ ተወካይ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጥባቸው ከ550 የማይበልጡ የምርጫ ክልሎች የሚኖሯት ሆኖ አከላለሉ የህዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ቁጥር መሠረት በማድረግ ይወሰናል፡፡ አነስተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚወከሉባቸውን የምርጫ ክልሎች ሳይጨምር ምርጫ ክልሎቹ ተቀራራቢ የሕዝብ ቁጥር ያላቸው ሆነው በመካከላቸው ያለው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ልዩነት ከ15% መብለጥ የለበትም፡፡

   ሐ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 54 መሠረት የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው ቁጥራቸው ከ20 የማያንሱ የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚወከሉባቸው የምርጫ ክልሎች ይኖራሉ፡፡

   መ. የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ በመሆኑ የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው ብሔረሰቦች ማንነትና ቁጥር ቀድሞ በሚዘጋጅ ግልፅ መስፈርት መሠረት በፌደሬሽን ምክር ቤት ይወሰናል፡፡ እነዚህን የምርጫ ክልሎች በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

   ሠ. የምርጫ ክልሎች ዝርዝር ቦርዱ በሚያቀርበው ጥናት መሠረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ከተወሰነ በኋላ የእጩዎች ምዝገባ ከሚጀመርበት እለት 150 ቀናት አስቀድሞ ለህዝብ ይገለፃል፡፡

   ረ የምርጫ ክልል አከላለልን በሚመለከት የፓርቲና የግል ዕጩ ተወዳዳሪዎችን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት የሚነሱ ቅሬታዎች ወይም ክርክሮች የምርጫ ክልሎች ዝርዝር ይፋ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርበው፡ምክር ቤቱ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡ በፌደሬሽን ምክር ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔው በተሰጠ በ15 ቀናት ውስጥ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱም በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2. በየደረጃው የሚካሄዱ የአካባቢ ምርጫዎች በየክልሉ ህግ መሠረት ለየምክር ቤቱ የሚመረጡትን አባላት ቁጥርና የመራጩን ብዛት መሠረት ያደረጉ ተመጣጣኝ የምርጫ ክልሎች በማቋቋም ይከናወናሉ፡፡

3. እያንዳንዱ የምርጫ ክልል እንደ አግባብነቱ በአዋጅ ቁጥር 1133/211 አንቀፅ 6 (1) ለስራ አመራር ቦርዱ አባልነት የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ 3 ሰዎችን የያዘ የምርጫ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

4. ቦርዱ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል የአገር ውስጥ ወይም የውጪ ታዛቢ ተወካዮች በቋሚነት ለማኖር ጥረት ያደርጋል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚደረገው የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ እና ምደባ በምርጫ ክልሉ ለሚወዳደሩ የፓርቲና የግል ዕጩዎች ግልጽ እንዲሆን እና የምርጫ አስፈጻሚዎች ምልመላም የፆታ ተዋጽኦን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

6. እያንዳንዱ ምርጫ ክልል በምርጫ ክልሉ ኃላፊ የሚደራጅ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚኖረው ሲሆን ኮሚቴው በምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል የሚመራ ሆኖ የየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑ መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ሁለት አባላት ይኖሩታል፡፡

7. የዚህን አንቀጽ አፈጻጸም በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 14. የምርጫ ክልል ስልጣንና ተግባራት

እያንዳንዱ የምርጫ ክልል የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት፡-

   ሀ. የምርጫ ቁሳቁሶችን ለምርጫ ጣቢያዎች ያሰራጫል፣

   ለ. ዕጩዎችን ይመዘግባል፡ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ዕጩዎች የመታወቂያ ካርድ ይሰጣል፣

2. ከምርጫ ጣቢያዎች የሚመጡ ሰነዶችና የምርጫ ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው መምጣታቸውን ያረጋግጣል፣ ይረከባል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣

3. ምርጫ ጣቢያዎች ተግባራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣

4. በህግ መሠረት ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ውሳኔ ይሰጣል፣

5. ከምርጫ ጣቢያ የመጡ የምርጫ ውጤቶችን በመደመር አሽናፊዎችን ከለየ በኂላ ጊዜአዊ ውጤት ለህዝብ ይፋ በማድረግ አስፈላጊ ቅጾችን በመሙላት ለቦርዱ ይልካል፣

6. የዕጩ ወኪሎችን ዝርዝር ለምርጫ ጣቢያዎች ያስተላልፋል፣

7. የምርጫ ክልሉን ሁለት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በዚህ ህግና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ያስመርጣል፣

8. በምርጫ ክልሉ የሚወዳደሩ የፖለቲካ ድርጅቶችን የጋራ ምክክር ያስተባብራል፣

9. የምርጫ ሂደትንና ውጤትን በተመለከተ ከምርጫ ጣቢያ ለሚመጡ አቤቱታዎች አፋጣኝ ምላሽ ወይም ውሳኔ ይሰጣል፣

10. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተመራጭነት መታወቂያ ለአሸናፊዎች ይሰጣል፣

11. ከቦርዱ ወይም ከክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## 15. የምርጫ ጣቢያዎች ስለማቋቋም

1. የምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ የአካል ጉዳተኞትን ልዩ ሁኔታ ጨምሮ የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በሚወስነው ስፍራ የሚቋቋሙ ሲሆን፤ አድራሻውም ለህዝብ የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ 15 ቀናት አስቀድሞ በይፋ ይገለጻል።

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ በተለይ በአርብቶ አደር አካባቢዎች የአርብቶ አደሩን ህዝብ አኗኗር መነሻ በማድረግ ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢያዎችን ሊያቋቁም ይችላል። በዚህ ጊዜ የሕዝቡን የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ተከትሎ የሚሰየሙትን ጣቢያዎች አድራሻ አስቀድሞ ለሕዝቡ ይገለጻል።

3. በይፋ ለሕዝብ የተገለጹ የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ፣ የድምፅ መስጫ እና የቆጠራ ሥራዎችን የሚስተናገድባቸው ብቸኛ ስፍራዎች ናቸው።

4. ቦርዱ ለምርጫው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምርጫ ጣቢያ ቦታዎችን ሊለዋውጥ ይችላል። ለውጡንም በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ለህዝብ ይፋ ያደርጋል።[1]

5. ወታደራዊ ካምፖች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ ቤተክርስትያናትና መስጊዶች፣ ሆስፒታሎች፣መጠጥ ቤቶች፣ የፖለቲካ ወይም የሀይማኖት ድርጅቶች ህንፃዎች፣ የግል

መኖሪያ ቤቶች የምርጫ ምዝገባና የድምፅ መስጫ ሥፍራ በመሆን ሊያገለግሉ አይችሉም፡፡

6. እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የሚያስተናግደው የመራጮች ብዛት ከአንድ ሺህ አምስት መቶ መብለጥ የለበትም፡፡

7. ለአንድ የምርጫ ጣብያ በተከለለ አካባቢ ከአንድ የምርጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይቻልም፡፡

8. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ እንደአግባብነቱ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀፅ 6 (1) ለቦርድ አባላት ምልመላ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አምስት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በአባልነት የያዘ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡ የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

9. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 8 መሠረት የሚደረገው የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላ ያታዊ ውክልናን ታሳቢ በማድረግ እንዲከናወን ሂደቱም በምርጫ ክልሉ የሚወዳደሩ ፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል ተወዳዳሪዎች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

10. እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በሚመደብ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሰብሳቢነት የሚመራ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፤ ኮሚቴው ከሰብሳቢው በተጨማሪ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በምርጫ ክልሉ ከተመዘገቡ መራጮች መካከል የሚመረጡ፤ የማንም ፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆኑና በመልካም ሥነ ምግባራቸውና ሰብእናቸው የታወቁ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት አባላት ይኖሩታል ፡፡ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

11. ቦርዱ በእያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ቢያንስ አንድ የሃገር ውስጥ ወይም የውጪ ታዛቢ በቋሚነት እንዲገኙ ጥረት ያደረጋል፡፡ የታዛቢዎቹ ስብጥር በተቻለ መጠን የፆታ ተዋጽዖን ፆታዊ ውክልናን ታሳቢ ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 16. የምርጫ ጣቢያ ስልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሚያከናውናቸው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

1. መራጮችን ይመዘግባል፣
2. ከምርጫ ክልሉ የሚላኩ የምርጫ ቁሳቁሶችን ተቀብሎ በጥንቃቄ ይይዛል፣
3. በዚህ አዋጅ መሠረት ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ምርጫ ያካሂዳል፣
4. በህጉ መሠረት የሚቀርቡለትን ቅሬታዎች ያስተናግዳል፣

5. የተሰጠውን የድምፅ ቆጠራ በማካሄድ ጊዜአዊ የምርጫ ውጤት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ለህዝብ ያሳውቃል፣

6 የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው እና ተጠብቀው ለምርጫ ክልሉ እንዲላኩ ያደርጋል፣

7. በዚህ ህግ አንቀጽ 15/10 እና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የምርጫ ጣቢያውን አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሁለት አባላት ያስመርጣል፣

8. በምርጫ ሂደት ለሚከሰቱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ፈጣን ምላሽ ይሰጣል፤ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣

9. ከቦርዱ፣ ከክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ወይም ከምርጫ ክልል የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## 17. በልዩ ሁኔታ የሚቋቋም የምርጫ ጣቢያ

1. ቦርዱ ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮች፣ ሲቪል ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ዜጎች፣ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች እንዲሁም በእስር ቤት የሚገኙ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መራጮቹ በሚገኙበት ቦታ ወይም አካባቢ ልዩ ምርጫ ጣቢያ ሊያቋቁም ይችላል። ከላይ የተጠቀሱት መራጮች ድምፅ የሚሰጡበትን ቦታ፣ ድምጻቸው የሚቆጠርበትን የምርጫ ክልል እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል።
2. ቦርዱ ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱት መራጮች ከምርጫው ቀን ቀደም ብለው እንዲመዘገቡና ድምጽ እንዲሰጡ በመወሰን በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው ውስጥ ሊያካትት ይችላል፡
3. ቦርዱ በውጪ ሃገር በመኖራቸው ወይም በሌላ ምክንያት በአካባቢያቸው መምረጥ ለማይችሉ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበት ልዩስርአት ሊዘረጋ ይችላል።ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት
## ስለምርጫ አፈጻጸም
## ምዕራፍ አንድ
## የመራጮች ምዝገባ

## 18. በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ. ኢትዮጵያዊ ከሆነ፣

ለ. በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ፣

ሐ. በምርጫ ክልሉ ቢያንስ ስድስት ወር የኖረ ከሆነ፣
በመራጭነት ሊመዘገብይችላል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተቀመጡት መስፈርቶች መሟላታቸው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት የሚረጋገጥ ይሆናል።

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ በታች የተመለከቱት በመራጭነት ሊመዘገቡ አይችሉም፡፡

ሀ. በአዕምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠበት ሰው፣

ለ. የመምረጥ መብቱ በህግ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የተገደበበት ሰው፡፡

## 19. የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ

1. የጠቅላላ ምርጫ ምዝገባ በአገር አቀፍ ደረጃ ቦርዱ በሚወስናቸው ቀናት የሚጀመርና የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ ቦርዱ የምዝገባ ቀናቱን ከመወሰኑ በፊት በምርጫው የሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ያማክራል፡፡

2. ቦርዱ የመራጮች ምዝገባ የሚጀመርበትን ዕለት በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው በማካተት ምዝገባው ከመጀመሩ ከ15 ቀን በፊት ጀምሮ በተከታታይ በመገናኛ ብዙሃንና በማስታወቂያዎች አማካይነት ለህዝቡ ይገልፃል፡፡

3. ቦርዱ ልዩ ሁኔታ ሲያጋጥም ልዩ የምዝገባ ቀን ሊወስን ይችላል፡፡

4. ማንኛውም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችለውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

5. ቦርዱ የአካባቢ ምርጫዎችን የምዝገባ ጊዜ ሰሌዳ የሚመለከተውን ክልል ህገ መንግስት ወይም ሌሎች ተፈጻሚነት ያላቸውን ህጎች መነሻ በማድረግ ያወጣል፡፡ በጊዜ ሰሌዳው ዝግጅትን በተመለከተ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ይመካከራል፡፡

## 20. የምዝገባ ቦታ

1. የመራጭ ምዝገባ በእያንዳንዱ ቀበሌ ውስጥ በሚቋቋሙና መራጮች ሄደው በሚመዘገቡባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ብቻ ይከናወናል፡፡ ስለሆነም ወደ ምርጫ ጣቢያ የሚመጣውን ተቀብሎ ከማስተናገድ በስተቀር ከምርጫ ጣቢያው ውጭ ቤት ለቤት እየዞሩ ወይም በየመንገዱ እየተዘዋወሩ ምዝገባ ማከናወን የተከለከለ ነው፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም በአርብቶ አደሮች አካባቢ እንደ አስፈላጊነቱ ተንቀሳቃሽ የምዝገባ ጣቢያ በማቋቋም ወይም ቤትለቤት በመሄድ የመራጮች ምዝገባ ማከናወን ይቻላል፡፡

3. እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የራሱ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል፡፡

## 21. የአመዘጋገብ ሥርዓት

1. ተመዝጋቢው በሚኖርበት የምርጫ ጣቢያ ማንነቱን የሚገልፅ የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት በመያዝ ለመመዝገብ ይችላል፡፡

2. የቀበሌ መታወቂያ ካርዱ ወይም ፓስፖርቱ ያልታደሰ ቢሆንም እንኳን ለምዝገባ ሊያገለግል ይችላል፡፡

3. የቀበሌ መታወቂያ ካርድ ማቅረብ ካልተቻለ በቅርቡ ፎቶግራፍ ተደርጎበት የተሰጠ እንደ የመንጃ ፈቃድ፣ የመኖሪያ የምስክር ወረቀት፣ ከውትድርና የተገለለበት ሰነድ፣ የትምህርት ቤት መታወቂያ የመሳሰሉ የመለያ ማስረጃዎች በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችሉ ሰነዶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

4. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የመለያ ማስረጃዎች በማይኖሩበት ወቅት መዝጋቢዎች መራጩን ለይተው የሚያውቁት ከሆነ ወይም በገጠር አካባቢ ሲሆን በባህላዊና ልማዳዊ ዘዴ ተመዝጋቢውን ለመለየት የሚቻልበት ሁኔታ ካለ ቃለ ጉባኤ ተይዞ ምዝገባው ይከናወናል፡፡

5. የምርጫ ጣቢያው በተቋቋመበት ቀበሌ ኗሪ የሆኑ ለረዥም ጊዜ መኖራቸው የተረጋገጠ ሦስት ግለሰቦች ነዋሪዎች በሚሰጡት ምስክርነት ማስረጃ አልባውን ተመዝጋቢ ለመለየት ከተቻለ ሂደቱ በቃለ ጉባኤ ተይዞ ምዝገባው ሊከናወን ይችላል፡፡

6. ለመራጭነት ብቁ የሆነ ሰው በተዘጋጀው የመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ይመዘገባል፡፡

7. በመራጭነት ለተመዘገበ ማንኛውም ሰው ሙሉ ስም ከነአያቱ፣ የሚኖርበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የምርጫ ጣቢያ፣ የቤት ቁጥር፣ መንደር ወይም ጎጥ፣ የመዝገብ ቁጥር፣ የምዝገባ ተራ ቁጥር፣ የመዝገብ ገፅ፣ የመራጩ ፊርማ፣ የመዝጋቢ ፊርማ፣ የተመዘገበበት ቀን ተሞልቶ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

8. የመራጮች ምዝገባ የሚከናወነው ከምርጫ አስፈጻሚዎች ቢያንስ ሦስቱ በጣቢያው ሲገኙ ነው፡፡

## 22. የመራጮች መዝገብ ይዘት

የመራጮች መዝገብ በሚከተሉት አርዕስቶች ሥር መረጃ ለመሙላት የሚያስችሉ ዓምዶች ይኖሩታል፣

1. የምዝገባ ተራ ቁጥር፣
2. የምዝገባ ቀን፣
3. የተመዝጋቢው ሙሉ ስም ከነአያት፣
4. የትውልድ ቀን እና ዓ.ም፣
5. ዕድሜ፣
6. ፆታ፣
7. አካል ጉዳተኝነት [የአካል ጉዳት (አለ/የለም)፣የአካል ጉዳተኝነት ሁኔታ፣ለጉዳተኛው የሚያስፈልግ እገዛ]
8. በምርጫ ክልሉ የኖረበት ጊዜ፣ (በወራት/በዓመት)
9. የምዝገባው ዕለት የፅህፈት ወይም የጣት ፊርማ፣
10. የምርጫ ዕለት የፅህፈት ወይም የጣት ፊርማ፣
11. የቤት ቁጥር/መንደር / ጎጥ/ የቦታው ልዩ መጠሪያ፣
12. ልዩ አስተያየት/ምርመራ የሚሠፍርበት አምድ፣
13. በልዩ ሁኔታ ለሚቋቋሙ የምርጫ ጣቢያዎች ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች በተጨማሪ የመራጮቹ የተለዩ ሁኔታዎች የሚመዘገቡበት ዐምዶች፣

## 23. የሰነዶች ስርጭትና ርክክብ

1. ቦርዱ በምርጫው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች በወቅቱ ለምርጫ ጣቢያዎች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡

2. ቃለ ጉባኤዎችን ጨምሮ በምዝገባ አገልግሎት ላይ የዋሉ ሰነዶች እና የመራጮች መዝገቦች ርክክብ ሥነ ሥርዓትና ጊዜ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

## 24. አንድ ጊዜ እና አንድ ቦታ ብቻ ስለመመዝገብ

1. ማንኛውም መራጭ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ ወይም በሌላ የምርጫ ጣቢያ ድጋሚ መመዝገብ የለበትም፡፡

2. አንድ መራጭ አንድ የመራጭነት መታወቂያ ካርድ ብቻ ይኖረዋል፡፡

3 ማንኛውም የመራጮች መታወቂያ ካርድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት መራጭ ከድምፅ መስጫው እለት በፊት በማንኛውም የምርጫ ጣቢያው የሥራ ጊዜ ፣ በድምፅ መስጫው እለት ከሆነ ደግሞ ምርጫ ሰዓቱ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ጣቢያው ሊያመለክት ይችላል፡፡ በምርጫ ጣቢያ ጽህፈት ቤቱም የአመልካቹ ማንነት ከመራጮች መዝገብ ጋር ተመሳክሮ እና ጉዳዩ በቃለ ጉባኤ ተይዞ በምትኩ ሌላ ካርድ ሊሰጠው ወይም ድምፅ እንዲሰጥ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## 25. ስለመራጮች መዝገብ መዘጋት

1. የቀኑ የምዝገባ ሥራ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ የዕለቱ የመጨረሻ ተመዝጋቢ ቁጥርና ቀኑን በተዘጋጀው የመፈራረሚያ ቅፅ ላይ ይሞላና የጣቢያው ምርጫ አስፈጻሚዎች ይፈራረሙበታል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 በተቀመጠው ሁኔታ የመራጮች ምዝገባ ወቅት እስኪጠናቀቅ ድረስ ምዝገባው ይቀጥላል፡፡ በምዝገባው የመጨረሻ ቀን በመዝገቡ ላይ ከመጨረሻው ተመዝጋቢ ቀጥሎ ባለው ክፍት ቦታ የጣቢያው ምርጫ አስፈጻሚዎች ተፈራርመውበት መዝገቡ ይዘጋል፡፡

3. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር መዝገቡ ከተዘጋና ከተፈራረሙበት በኋላ በመዝገቡ ላይ አዲስ መራጭ አይመዘገብም የሚሰፍር ወይም የሚፃፍ ነገርም አይኖርም፡፡

## 26. የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልፅ ስለማድረግ

1. የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለ10 ቀናት ይፋ ወጥቶ ህዝብ በግልፅ እንዲያየው ይደረጋል፡፡
2. በጣቢያው የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች እንዲሁም የግል ተወዳዳሪዎች ወይም ተወካዮቻቸው ለምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ጥያቄ በማቅረብ የመራጮች መዝገቡን መመልከት ይችላሉ፡፡

3. ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ የመራጮች መዝገብ ወደ ቦርዱ ክልል ጽህፈት ቤት ወይም ለምርጫ ጣቢያው ቅርብ የሆነ የበታች እርከን የምርጫ ጽቤት ተወስዶ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

4. ቦርዱ የምዝገባ ሂደቱ ከተጠናቀቀ እና ተያያዥ አቤቱታዎች ውሳኔ ካገኙ በሁዋላ የመራጮችን መዝገብ ግልባጭ ለተወዳዳሪዎች ሊሰጥ ይችላል ፡፡ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 27. የምዝገባ ተቃውሞን በተመለከተ

1. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በምዝገባ ላይ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የቀረበውን አቤቱታ ተመልክቶ አቤቱታው የቀረበበት ሰው መልስ እንዲሰጥ ካደረገ በኂላ በአምስት ቀን ውስጥ ውሳኔ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

## 28. ከምዝገባ ስለመሰረዝ

1. ማንኛውም ተመዝጋቢ በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል ወይም በበቂ ማስረጃ ካልተረጋገጠ ወይም በማጭበርበር የተመዘገበ ወይም በድጋሚ የተመዘገበ ወይም የሞተ ካልሆነ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት በተሰጠ የፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ መብቱ የተገደበ ካልሆነ በስተቀር በሚቀርብ ተቃውሞ ምክንያት ከመራጭነት ምዝገባ አይሰረዝም፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ ሲከሰት ፍርድ ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ እድሮች ወይም ሌሎች ስለጉዳዩ እውቀት ያላቸው የህብረተሰቡ አባላት ሁኔታው እንደተከሰተ ወዲያውኑ ለቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ለምርጫ ክልል ወይም ለየምርጫ ጣቢያ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡

3. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ወይም የምርጫ ክልሎች ወይም የምርጫ ጣቢያዎች ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት መረጃ እንደደረሳቸው በመራጭነት የተመዘገበው ሰው እንዲሰረዝ ማድረግ አለባቸው፡፡

## 29. ቋሚ የመራጮች መዝገብ

1. ቦርዱ ለያንዳንዱ የምርጫ ክልል ቋሚ የመራጮች መዝገብ የሚዘጋጅበት እንዲሁም በየጊዜው የሚስተካከልበትና የሚከለስበት ሥርአት እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

2. የመራጮች መዝገብ በክልልና ከዚያ በታች ባሉ እርከኖች በሚኖሩ የቦርዱ ጽህፈት ቤቶች በቦርዱ በሚሰየም ባለሙያ የሚመራና ከክልል መንግስታት ጋር በመመካከር እንዲሁም ከማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለስልጣን እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በመቀናጀት የሚዘጋጅና በየጊዜው የሚከለስ ይሆናል፡፡

3. የመራጮች መዝገብ አዘገጃጀት እንዲሁም የመዝገቡ አያያዝና አከላለስ ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የዕጩዎች ምዝገባ

### 30. የእጩ የምዝገባ ቦታ

የእጩ ምዝገባ ከምርጫው ዕለት ቢያንስ 90 ቀን አስቀድሞ ቦርዱ ለእጩዎች ምዝገባ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በምርጫ ክልሎች ይከናወናል፡፡

### 31. ለእጩነት የሚያበቁ መመዘኛዎች

1. ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ. ኢትዮጵያዊ የሆነ እና ለመመረጥ የተመዘገበ፣

   ለ. በምዝገባ ዕለት እድሜው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው፣

   ሐ. ከምርጫው እለት አስቀድሞ በምርጫ ክልሉ ውስጥ በመደበኛነት አንድ አመት ከኖረ ወይም የትውልድ ቦታው በእጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት የምርጫ ክልል ውስጥ ከሆነ ወይም ከተማው ወይም ወረዳው ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎችን የሚያቅፍ ከሆነ በከተማው ወይም በወረዳው ውስጥ ለሁለት ዓመት በመደበኛነት የሠራ፤ በዚያው ከተማ ወይም ወረዳው በፈለገው የምርጫ ክልል፣

   መ. በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገፈፈ፣

   ሠ. በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው መሆኑ ስልጣን ባለው አካል

   ረ. ለውድድር የቀረበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግል የቀረበ እጩ ቦርዱ በዚህ አዋጅና መሠረት የሚያወጣውን የምርጫ ሥነ ምግባር እና ደንብተቀብሎየፈረመ፣
   በእጩነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 “መ” የተደነገገው መመዘኛ፡-

   ሀ. በሥራ ወይም በትምህርት ምክንያት ከምርጫ ክልሉ ውጭ የነበረንሰው፣

ለ. ከዚህ በፊት በምርጫ ክልሉ ተመርጦ በመስራት ላይ ያለን ሰው አይመለከትም፡፡

3. ከላይ ከተደነገገው መመዘኛ በተጨማሪ በግል የቀረበ እጩ በአካባቢው መስተዳድር የተረጋገጠ እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በላይ ከሆናቸው እና መምረጥ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወይም አግባብ ባለው ህግ መሠረት ካልተከለከሉ የምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች ውስጥ ከአምስት ሺህ የማያንስ የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት፡፡

4. በግል እጩዎች የሚቀርቡ የድጋፍ ፊርማዎች የሚረጋገጡበት መንገድ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 64 እና 65 መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ የሚቀርቡ የመስራች አባላት ፊርማዎች ትክክለኝነት ከሚረጋገጥበት መንገድ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል፡፡

5. የግል እጩው ድጋፉን ያልሰጠ ሰው የሰጠ በማስመሰል፣ በሃሰት ስምና ፊርማ በማዘጋጀት፣ የሌለ ሰው እንዳለ በማስመሰል ወይም በሌላ የተጭበረበረ መንገድ መረጃ ማቅረቡ በማናቸውም ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት ከተረጋገጠበት አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የእጩነት ምዝገባ ማመልከቻው ውድቅ ሆኖ ወይም ምዝገባው ተሰርዞ ለሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት በግል እጩነትም ሆነ በፖለቲካ ፓርቲ አመራር ወይም አባልነት እንዳይሳተፍ ይደረጋል፡፡

## 32. የእጩ አቀራረብ

1. ማንኛውም በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚካሄድ ምርጫ መስፈርቱን የሚያሟላ እጩ በማቅረብ ሊወዳደር ይችላል፡፡

2. በንኡስ አንቀጽ አንድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች ሁሉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31(1) የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላታቸውን ከማረጋገጥ በተጨማሪ እንዳንዱ እጩ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወዳደር ከሆነ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ከሚኖሩ መራጮች ሶስት ሺህ የድጋፍ ፊርማ፤ ለክልል ምክር ቤት የሚወዳደር ከሆነ አንድ ሺህ አምስት መቶ የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

3. በፖለቲካ ድርጅት ተወክለው የሚወዳደሩ እጩዎችን ዝርዝር ለቦርዱ የሚያሳውቀው የድርጅቱ፣የግንባሩ ወይም የቅንጅቱ ሀላፊ ወይም ወኪሉ ይሆናል፡፡

4. በፖለቲካ ድርጅት ተወክሎ ለሚቀርብ እጩ በፓርቲው መወከሉን እና በእጩነት ለመቅረብ መስማማቱን የሚገልጽ ሰነድ ከእጩነት ማስረጃው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

5 የፖለቲካ ፓርቲዎች ግንባር ወይም ቅንጅት በአንድ የምርጫ ክልል ለአንድ የምክር ቤት መቀመጫ ማቅረብ የሚችለው አንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ ይሆናል፡፡

6. ማንኛውም እጩ ተወዳዳሪ በግንባር በመቅረብ መመዝገብ አለበት፡፡በግንባር ቀርቦ መመዝገብ ካልቻለ ለእጩነት የሚያበቁ መስፈርቶች ማሟላቱን የሚያረጋግጡ ተጨባጭ የሰነድ እና እንደአግባብነቱ የሰው ማስረጃዎች ቀርበው እጩውን ባቀረበው ፖለቲካ ፓርቲ አማካይነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡
7. የእጩዎች ምዝገባ ከምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ቢያንስ ሁለቱ ባሉበት መከናወን አለበት፡፡

## 33. በምርጫ ስለሚወዳደሩ የመንግስት ሰራተኞች

1. ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ፡-

ሀ. በግሉ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በመሆን ለምርጫ መወዳደር ይችላል፡:
ለ. በምርጫ የሚወዳደሩ የመንግሥት ሠራተኞች በዕጩነት ከተመዘገቡበት ጊዜ ጀምሮ የምርጫው ሂደት እስከሚጠናቀቅ በጊዜአዊነት ከስራ ገበታቸው መልቀቅ ይኖርባቸዋል፡፡

ሐ. ከላይ በንኡስ አንቀፅ ለ በተመለከተው ሁኔታ ከስራ ገበታው በጊዜያዊነት ስራ የለቀቀ ዕጩ ምርጫው እስኪጠናቀቅ ባለው ጊዜ ውስጥ የሚከፈለው ደሞዝ እና ጥቅማ ጥቅም አይኖርም፤ በማንኛውም የቀጣሪው የመንግስት መ/ቤት ንብረትም መገልገል አይፈቀድለትም፡፡

መ. ከላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በእጩ ተወዳዳሪነት ተሳትፎ አሸናፊ ያልሆነ የመንግስት ሰራተኛ ወደ ስራ መደቡ ያለቅድመ ሁኔታ የመመለስ እንዲሁም በስራው ውጤታማነት ላይ ተመስርቶ ማግኘት ያለበትን እድገት ወይም ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት አለው፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ዳኞች፣ ወታደሮች፣ ፖሊስ እና ሌሎች የጸጥታ ሃይሎች፣ የደህንነት ሰራተኞች፣ እና የቦርዱ ሰራተኞች በግል ወይም የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ ሆነው ከቀረቡ የያዙትን የመንግስት ሥራ መልቀቅ አለባቸው፡፡፡

3. ዳኞች፣ ወታደሮች፣ ፖሊስ እና ሌሎች የጸጥታ ሃይሎች፣ የደህንነት ሰራተኞች እና የቦርዱ ሰራተኞች በምርጫ ውድድር ጊዜ ማንኛውንም ተወዳዳሪ ለማስመረጥ በመደገፍ፣ በመናገር፣ በመፃፍና በመሳሰሉት ተሳታፊ መሆን የለባቸውም፡፡

3. ማንኛውም ወታደር ወይም ፖሊስ በፖለቲካ ድርጅት ስብሰባ ወይም በምርጫ እንቅስቃሴ መለዮውን አድርጎ መሳተፍ አይችልም፡፡

## 34. ለግል እጩ የድጋፍ ፊርማ ስለመስጠት

አንድ የመምረጥ መብት ያለው ነዋሪ በምርጫ ክልሉ ለውድድር ከቀረቡት መቀመጫዎች ቁጥር እጥፍ በላይ ለሆኑ እጩዎች የድጋፍ ፊርማ መስጠት አይችልም፡፡

## 35 የእጩነት የመታወቂያ ካርድ ስለ መስጠት

1. ከላይ በአንቀጽ 32 መሠረት ለውድድር የሚቀርበው እጩ ከተለየ በኋላ በዕጩዎች መመዝገቢያ ቅፅ ስሙ እንዲሰፍር ተደርጎ የእጩነት መታወቂያ ካርድ ይሰጠዋል፡፡

2. የፖለቲካ ድርጅት እጩዎች የእጩነት መታወቂያ ካርድ ለእጩዎቹ ወይም ላስመዘገባቸው ድርጅት ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 36. እጩዎችን ለህዝብ ስለማሳወቅ

እጩዎች በዚህ አዋጅ መሠረት ከተለዩ በኋላ የዕጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የተወዳዳሪ እጩዎችን ስም ዝርዝር ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

## 37. የእጩዎች የመለያ ምልክቶች

1. ማንኛውም እጩ የሚወዳደርበትን መለያ ምልክት ሊያቀርብ ወይም ቦርዱ ከሚያዘጋጃቸው መለያ ምልክቶች መርጦ ሊይዝ ይችላል፡፡

2. የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች በሁሉም የምርጫ ደረጃዎች አንድ ዓይነት ምልክት ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

3. የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች ለየምክርቤቱ ምርጫ በሁሉም የምርጫ ክልሎች አንድ ዓይነት መለያ ምልክት መጠቀም አለባቸው፡፡

4. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ባለፈው ምርጫ የተጠቀመበትን ምልክት ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡

5. በምርጫ መለያ ምልክት ዙርያ በሚነሱ አለመግባባቶች ምክንያት አቤቱታ ሲቀርብለት የስራ አመራር ቦርዱ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6. ማንኛውም መለያ ምልክት፡-

   ሀ. ከሌሎች እጩዎች መለያ ምልክት ጋር የማይመሳሰል፣

   ለ. በብሔር ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥላቻና ግጭት ሊቀሰቅስ ከሚችል ነገር ወይም ሁኔታ ጋር ግንኙነት የሌለው፤

   ሐ. የጦርነት ወይም የሌላ ህገወጥ ድርጊት መልዕክት የማያስተላልፍ፣

   መ. ከፌደራልም ሆነ ከክልል መንግስታት ሰንደቅ አላማ ወይም አርማ ወይም ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች አርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች

ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፣

ሠ. የህዝብን ሞራል፣ መልካም ሥነ ምግባር እና የመሳሰሉትን የማይጥስ መሆን አለበት፡፡

7. ቦርዱ በድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ የእጩዎች ምስልና የመለያ ምልክቶችን አቀማመጥ፣ ቅደም ተከተልና እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች እና የግል እጩዎች ግልጽ በሆነ መንገድ በመመሪያ ይወስናል፡፡

## 38. የእጩ የመለያ ምልክት መለወጥና መተካት

1. ቦርዱ በአንቀጽ 37 መሠረት አንድን የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ መለያ እንዲለውጥ ለማዘዝ ይችላል፡፡

2. የእጩ መለያ ምልክት እንዲለወጥ በቦርዱ ሲወሰን የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ አምስት ቀን ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲው ወይም ለግል እጩው ውሳኔውን እንዲያውቀውና ተለዋጭ ምልክት እንዲያቀርብ ወይም እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡

3. የፖለቲካ ፓርቲም ሆነ የግል እጩ ቀደም ሲል የመረጠውን ምልክት በሌላ ለመለወጥ ሲፈልግ የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ በአስር ቀናት ውስጥ ለውጡን ለቦርዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 39. የእጩዎች ከውድድር መውጣትና መተካት

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ከውድድር ራሱን ሊያገል ይችላል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ከውድድር ራሱን ያገለለ የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ለወከለው የፖለቲካ ፓርቲ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

3. የፖለቲካ ፓርቲ እጩውን መለወጥ ወይም መተካት የሚችለው እጩው ራሱን ካገለለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ወይም እጩው ራሱን ያገለለው የእጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ካለቀ በኋላ ከሆነ ከድምጽ መስጫው ቀን ከአንድ ወር በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 32 ላይ የተቀመጠው መስፈርት በተተኪነት በሚቀርብ እጩ ላይም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 40. የእጩ መሞት

1. የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ እጩ ተወዳዳሪ የእጩ ምዝገባ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሞተ እንደሆነ እጩው የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት ከድምጽ መስጫው ቀን አንድ ወር በፊት ባለው ጊዜ ውስጥ ሌላ እጩ ሊተካ ይችላል፡፡

2. አንድ ወደ ውድድር የገባ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በተባለው ጊዜ ውስጥ ተተኪ ካላቀረበ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ እጩ የሞተው የምርጫው ቀን ሊደርስ ከአንድ ወር ያነሰ ጊዜ ሲቀረው እንደሆነ ምርጫው ባሉት እጩዎች መካከል በተያዘለት ጊዜ ውስጥ ይከናወናል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተገለፀው ቢኖርም እጩ የሞተበት የፖለቲካ ፓርቲ ተተኪ እጩ ማቅረብ እንደማይችል በጽሑፍ የገለፀ እንደሆነ የምርጫው ውድድር ባሉት እጩዎች መካከል በተያዘለት ጊዜ ሊካሄድ ይካሄዳል፡፡

## 41. በአንድ ምርጫ ክልል ብቻ ስለመወዳደር

1. አንድ ሰው በእጩ ተወዳዳሪነት መቅረብ የሚችለው በአንድ የምርጫ ክልል ብቻ፥ ለአንድ የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት ወንበር ብቻ ይሆናል፡፡

2. አንድ እጩ ተወዳዳሪ በእጩዎች ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከአንዱ የምርጫ ክልል ወደ ሌላው የምርጫ ክልል ተዛውሮ በህጉ መሠረት እንደ አዲስ ተመዝግቦ ለመወዳደር ይችላል፡፡ አፈፃፀሙ በቦርዱ ይወሰናል፡፡

## 42. የእጩዎች ልዩ መብት

1. እጩዎች ከባድ ወንጀል ሲፈፅሙ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር ምርጫው እስከሚጠናቀቅ ድረስ በወንጀል ተጠርጥረው ተከሰው አይያዙም፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 እንደተጠቀሰው እጅ ከፍንጅም ባይሆን ዕጩዎች ህገወጥ ድርጊት የፈፀሙ እንደሆነ ሕጋዊ እርምጃ ሊወሰድባቸው የሚችለው የምርጫው ውጤት በቦርዱ አማካይነት በይፋ ለህዝብ ከተገለፀ በኂላ ብቻ ይሆናል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም አሸናፊው ሰው በምርጫ ወቅት በፈፀመው ወንጀል የሚጠየቀው በሚመለከተው ምክር ቤት የህግ ከለላው ሲነሳ ብቻ ነው፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>
## <u>የምርጫ ዘመቻ</u>

## 43. የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ ስለማካሄድ

1. አንድ እጩ ተወዳዳሪ በእጩነት ተመዝግቦ መታወቂያ ካገኘበት ቀን አንስቶ ምርጫው አራት ቀን እስኪቀረው ድረስ ከአስተዳደሩም ሆነ ከማዘጋጃ ቤት ፈቃድ መጠየቅ ሳያስፈልገው፥ በጽሑፍ በማሳወቅ ብቻ እና ሕጋዊ ግዴታዎቹን በማክበር በራሱም ሆነ በደጋፊዎቹ አማካይነት የድጋፍ ስብሰባዎችን የመጥራት ወይም ሰላማዊ ሰልፍ

የማደራጀት መብት አለው፡፡ እንዲሁም ለምርጫ ውድድሩ ይጠቅሙኛል ያላቸውን መረጃዎች ከቦርዱ እንዲሁም ከሌሎች የመንግስት ተቋማት የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡

2. እጩዎችና ደጋፊዎቻቸው ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የሚያካሂዱት የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ ከአራት ቀናት በፊት መጠናቀቅ አለበት፡፡

3. የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ህገመንግስቱና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ህጎች፣ የመራጮችን መብት፣ የሌሎች እጩዎችን የመወዳደር መብት በማክበር በሰላማዊና በዴሞክራሲያዊ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡

4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱት መብቶች በህግ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውጭ ተፈፃሚ ሊደረጉ አይችሉም፡፡

5. ምርጫውን ሰላማዊ እና ፍትሐዊ ለማድረግ እንዲቻል ቦርዱ የምርጫ ቅስቀሳ የሥነ ምግባር ደንብ ያወጣል፡፡

## 44. የብዙኃን መገናኛ አጠቃቀም

1. በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉትን ብዙኃን መገናኛ ማለትም ሬድዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦችን የፓለቲካ ፓርቲዎችና ደጋፊዎቻቸው ያለ አድልዎ የመጠቀም መብት አላቸው፡፡
2. እጩዎች በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ነፃ የአየር ጊዜ አግኝተው የመጠቀም መብት አላቸው፡
3. መንግስት ብዙኃን መገናኛ አጠቃቀም ቦርዱ ከኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶችን ባሳተፈ አካሄድ በሚያወጣው የድልድል መመሪያ መሠረት ይከናወናል፡፡

4. የብዙኃን መገናኛ አጠቃቀም፥ የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ እና ተያያዥነት ጉዳዮችን የሚመለከቱ የሥነ ምግባር እና የአፈጻጸም መርሆችንቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

## 45. የመንግስት አካላት ግዴታ

የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴዎችን ለማሳካት በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አካላት ኃላፊዎች የሚያስተዳድሯቸውን የሬድዮና የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፣ ጋዜጦችና እንዲሁም የስብሰባ አዳራሾች፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎችና ደጋፊዎቻቸው ያለአድልዎ እንዲገለገሉባቸው ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው፡፡ አፈጻጸሙን በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 46. የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ የማይደረግባቸው ቦታዎች

1. የሚከተሉት ቦታዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ/ዘመቻ አይደረግባቸውም፣

   ሀ. ቤተክርስትያኖች፣

   ለ. መስጊዶች፣

   ሐ. ወታደራዊ ካምፖች እና ፖሊስ ጣቢያዎች፣

   መ. የመማር ማስተማር ሂደት ተግባር እየተከናወነ በሚገኝበት ወቅት በትምህርት ቤቶች እና በትምህርት ቤቶች አካባቢ በ200 ሜትር ርቀት ዙሪያ፣

   ሠ. ህዝብ የእለትተለት ግብይት በሚፈፅምባቸው እና በተወሰኑ ቀናት በገጠርም ሆነ በከተማ በይፋ ገበያ እየተካሄደ በሚገኝባቸው ቦታዎች በ200 ሜትር ዙሪያ ክልል፣

   ረ. የመንግስት ወይም የህዝብ መደበኛ ሥራ በመከናወን ላይ የሚገኙባቸው የመንግስትና የህዝብ ተቋማት ሥራቸውን በሚያከናውኑበት መደበኛ የሥራ ሰዓት እና ቦታ፣

   ሰ. ህዝባዊ ስብሰባ እየተካሄደ ባለባቸው ቦታዎች እና አካባቢዎች፡፡

2. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## ስለ ድምፅ አሰጣጥ

## 47. ስለምርጫ ጣቢያ ሥራ መጀመር

1. የድምጽ መስጠት ሂደት በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ በሚወስነው ቀን አንድ ላይ ይጀመራል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚመለከታቸው ምርጫ ጣቢያዎች ስራቸውን በተለየ ቀን እንዲጀምሩ ቦርዱ ሊወስን ይችላል፡፡

3. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የድምፅ አሰጣጡ ሥራ፡-

   ሀ. የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ ወኪሎች፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ታዛቢዎች፣ እና የምርጫ አስፈፃሚዎች በተገኙበት፣ እና

ለ. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የድምፅ መስጫ ሳጥን ባዶ መሆኑን ከላይ በ “ሀ” ለተገለፁት አካላት በማሳየት የምርጫ ሳጥኑ በተዘጋጀው ማሸጊያ ታሽጎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታና በግልጽ ስፍራ ከተቀመጠ ወይም ከተሰቀለ በኋላ ስለ አጀማመሩ ቃለ ጉባዔ ተይዞ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅፅ ላይ ከተሞላ በኋላ ይጀመራል፡፡

## 48. የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነት

1. የምርጫ ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት አስተማማኝ ጥበቃ ተደርጎላቸው ደኅንነታቸው ተጠብቆ መዘጋጀት አለባቸው፡፡

2. ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች እና የግል እጩ ወኪሎች ከቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትእና ከተፈቀደላቸው የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር መራጮች ያልሆኑና ድምፅ የሰጡ ሰዎች በምርጫ ጣቢያው ክልል ውስጥ መገኘት የለባቸውም፡፡

3. ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያው አምስት መቶ ሜትር ዙርያ መለስ ርቀት ውስጥ በስካር መንፈስ ውስጥ ሆኖ፣ የጦር መሳሪያ ይዞ ወይም በሌላ በማናቸውም ፀጥታን በሚያደፈርስ ሁኔታ ውስጥ መገኘት የለበትም፡፡ በዚህ ሁኔታ ከተገኝም የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የጸጥታ ሃይሎችን ድጋፍ በመጠየቅ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያ ደህንነት እንዲከበር የማድረግ ኃላፊነት በዋናነት የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ይሆናል፡፡ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ወይም የምርጫ ጣቢያ ታዛቢዎች የጣቢያውን ደህንነት ለማስከበር የፖሊስ ኃይል እንደሚያስፈልግ ካመኑ እንዲመደብላቸው የሚመለከተውን አካል መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፣ ታዛቢዎች እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል እጩ ወኪሎች ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡት በምርጫ ጣቢያ ኃላፊዎች አማካይነት ይሆናል፡፡

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ ለመግባት ያልተፈቀደለትን ግለሰብ ወይም የምርጫውን እንቅስቃሴ ለማወክ የሞከረን ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጣ ሊያዝ ይችላል፡፡ ግለሰቡ ትዕዛዝ አክብሮ ያልወጣ እንደሆነ የፖሊስ ኃይል ጠርቶ ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ ፖሊሱም ይህን ተግባሩን እንደፈፀመ ከምርጫ ጣቢያው ወጥቶ ወደ ምድብ ቦታው ይሄዳል፡፡

6. በምርጫ ጣቢያ ወይም በምርጫ ክልል ኃላፊ የምርጫ ደህንነትን የማስከበር ጥያቄ የቀረበለት ማንኛውም የፖሊስ ወይም የጸጥታ አካል ወይም ሌላ ሰው በአዋጅ ቁጥር 1133 …አንቀፅ 27 በተደነገገው መሠረት የመተባበር፣ ፈጣን ምላሽ የመስጠት እና የማስፈጸም ግዴታ አለበት፡፡

7. ሕጋዊነቱ አጠራጣሪ የሆነ ሰነድ ይዞ በምርጫ ጣቢያ ስለመገኘቱ አሳማኝ ጥቆማ የቀረበበትን ሰው የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል እጩ ወኪሎች እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት ተጠርጣሪው ሊፈተሸ ይችላል፡፡ ጥርጣሬው እውነት ሆኖ ከተገኘም አስፈላጊ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፡፡

## 49. የድምፅ መስጫ ሰአት

1. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የድምጽ መስጫ ሰዓት ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰአት ድረስ ይሆናል፡፡

2. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ የድምፅ መስጫ ሰዓት የወሰነ እንደሆነ በልዩ ሁኔታ የተወሰነውን የድምፅ መስጫ ሰአት ከምርጫው እለት ቢያንስ ሁለት ቀን አስቀድሞ ህዝቡ በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

3. የድምጽ መስጫ ሰአት ሲያበቃ የምርጫ ጣቢያው ይዘጋል፡፡ ሆኖም በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብተው ድምፅ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ ያሉ መራጮች ድምፅ መስጠት አለባቸው፡፡

4. ከላይ በንኡስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም ቦርዱ የምርጫው ነፃና ፍትሃዊነት ይበልጥ ያሰፍናል ብሎ ካመነ የድምፅ መስጫ ሰአቱን ሊያራዝም ይችላል፡፡

5. የምርጫ ጣቢያዎች ለምርጫ ከመከፈታቸው በፊትም ሆነ ድምፅ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጉ በኋላ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከህዝብ ከተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት፤ ከእጩ ተወካዮች እና ከተፈቀደላቸው የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም፡፡

## 50. ድምፅ ስለመስጠት

1. ማንኛውም መራጭ በአካል በመገኘት በሙሉ ነፃነት ድምፅ ይሰጣል፣

2. እያንዳንዱ መራጭ ድምፅ የሚሰጠው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፣

3. ማንኛውም መራጭ በመራጭነት በተመዘገበበት የምርጫ ጣቢያ ብቻም ቢሆን ድምፅ ለመስጠት የሚችለው፡-

   ሀ. የመራጮች መታወቂያ ካርድ ሲኖረው፣

   ለ. በመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ሰፍሮ ሲገኝ፣እና

   ሐ. ድምፅ ያልሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፣

4. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ሁሉም መራጮች በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ ድምፃቸውን ይሰጣሉ፡፡

## 51. ድምፅ የመስጠት ሂደት

1. እያንዳንዱ መራጭ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱን ለምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች ካስረከበ በኂላ የምርጫ አስፈፃሚዎች የመራጩን ማንነት ባቀረበው ማስረጃ መሠረት ይለያሉ፡፡

2. የመራጩ ማንነት ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ከተለየና ቀደም ሲል ያልመረጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በኂላ በመራጮች መዝገብ ውስጥ ለፊርማ በተዘጋጀው አምድ ላይ እንዲፈርም ይደረጋል፡፡

3. መራጩ በመዝገብ ላይ ከፈረመ በኂላ አውራጣቱን፣ አውራጣት ከሌለው ማንኛውንም ሌላ ጣት በተዘጋጀው የማይለቅ ቀለም እንዲቀባ ከተደረገ በኂላ የድምፅ መስጫ ወረቀት ተሰጥቶት ወደ ሚስጢር ድምፅ መስጫው ክፍል ይገባል፡፡ መራጩ ጣቶች የሌሉት ከሆነ የምርጫ አስፈፃሚዎች አለመምረጡን ካረጋገጡ በኂላ በቀላሉ የሚታይ ቦታ ላይ የማይለቅ ቀለም ይቀባና እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡

4. መራጩ ወደ ምስጢር ድምጽ መስጫው ክፍል ገብቶ የሚመርጠውን እጩ መለያ ምልክት በሚገኝበት ባለአራት ማዕዘን ቦታ ላይ የ"x" ወይም ሌላ የማያሻማ ምልክት ካደረገበት ወይም በጣት አሻራው ከፈረመበት በኂላ የድምጽ መስጫ ወረቀቱን አጥፎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታ በግልጽ ስፍራ በተቀመጠው የድምፅ መስጫ ሳጥን ወይም ኮሮጆ ውስጥ ያስገባል፡፡

4. የማያነቡና የማይፅፉ መራጮች ከጣቶቻቸው አንዱን ለዚህ በተዘጋጀው ቀለም ከነከሩ በኂላ ከሚመርጡት ዕጩ መለያ ምልክት ትይዩ በሚገኘው ባለ አራት ማዕዘን ክፍት ቦታ ላይ የጣት አሻራቸውን በማሳረፍ ድምፅ ይሰጣሉ፡፡

5. መራጩ የተሰጠውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ባግባቡ ሳይጠቀምበት የቀረ ወይም የተበላሸበት እንደሆነ የተበላሸውን መልሶ በምትኩ ሌላ በመቀበል ድምፅ ለመስጠት ይችላል፡፡

6. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ከላይ በንኡስ አንቀፅ 6 መሠረት ተመላሽ የሆነውን የድምፅ መስጫ ወረቀት የተለየ ምልክት ሰጥቶ ወይም "የተበላሸ" የሚል ጽሑፍ በጀርባው ላይ ጽፎበት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ይከተዋል፡

7. ቦርዱ የድምጽ አሰጣጡና እንዲሁም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 መሠረት የድምጽ ቆጠራው በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲከናወን ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይኸውም ከተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመመካከር የሚደረግ ሲሆን ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 52. ድጋፍ የሚፈልጉ መራጮችን በተመለከተ

1. አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ነፍሰ ጡሮች በምዝገባም ሆነ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፡፡

2. በምርጫ ድምፅ አሰጣጥ ምልክት ለማድረግና የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ወደ ድምፅ መስጫው ሳጥን ለመክተት እርዳታ የሚያስፈልገው ማንኛውም መራጭ የሚረዳውን ሰው እራሱ የመወሰን መብት አለው፡፡ ምርጫ አስፈጻሚው መራጩ መብቱን አውቆ እንዲጠቀምበት ለማድረግ በተቻለው ዓቅም ያስረዳዋል፡፡ ዝርዝሩም በህግ ይወሰናል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በድጋፍ ፈላጊው የተመረጠው ሰው ዕድሜ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ሆኖ እጩ ወይም የእጩ ተወካይ መሆን የለበትም፡፡

## 53. ድምፅ የመስጠት ሂደት የማይቋረጥ ስለመሆኑ

1. ድምፅ የመስጠት ሂደት ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም፣

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

   ሀ. የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በተለያዩ አስገዳጅ ምክንያቶች ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ከተቋረጠ በኋላ ሁኔታው መስተካከሉ በምርጫ አስፈፃሚዎች ከታመነበት በቃለ ጉባኤ ተይዞ ወዲያውኑ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ሊቀጥል ይችላል፡፡

   ለ. የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ የተቋረጠበት ምክንያት ከአቅም በላይ ሆኖ ሊስተካከል ካልቻለ ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ባለበት ቆሞ ወዲያውኑ አጠቃላይ ሁኔታው ለበላይ ምርጫ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ይደረጋል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሠረት የተቋረጠ የድምፅ መስጠት ሂደት ቦርዱ በሚወስነው መሠረት በሌላ ጊዜ ይካሄዳል፡፡

## 54. ድምፅ መስጠትን ስለመቃወም

1. ለማንኛውም መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት ድምፅ በመስጠት ሂደት ላይ ያለው ሰው ግለሰቡ ድምጽ የመስጠት መብት የሌለው ወይም በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት ያልተመዘገበ ነው በማለት የእጩ ተወካይ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. አንድ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ቢከለከል ራሱ ወይም ከእጩ ተወካዮች አንዱ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

3. የእጩ ተወካይ ወይም መራጩ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተደነገጉት የመቃወሚያ ነጥቦች ውጭ በሆነ ምክንያት በማንኛውም የምርጫ አስፈፃሚ፣ የእጩ ተወካይ ወይም በሌላ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በተገኘ ሰው አግባብ ያልሆነ ድርጊት ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ የቀረበውን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ አቤቱታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል ውሳኔውን በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በዚህ አንቀፅ መሠረት የቀረቡ ቅሬታዎችንና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ መልሶችን በፅሁፍ አስፍሮ በመረጃነት ይይዛል፡፡

## 55. ጊዜያዊ ድምፅ ስለመስጠት

1. ከላይ በአንቀጽ 54 መሠረት ድምፅ እንዳይሰጥ ተቃውሞ የቀረበበት ሰው ጊዜያዊ ድምፅ መስጠቱ አስፈላጊ ነው ብሎ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ካመነ መራጩ ለዚህ በተዘጋጀው ፖስታ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 መሠረት የተሰጠ ጊዜያዊ ድምፅ በአንቀፅ 153---- መሠረት ውሳኔ እንዳገኘ በቆጠራ የሚካተት ወይም ውድቅ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 56. ስለ ድምፅ መስጫ ወረቀት

1. ቦርዱ ለእያንዳንዱ የምርጫ አይነት መራጩ በግልጽ ሊረዳው የሚችል እስከሚቻለው ድረስ ለማጭበርበር የማይመች የድምፅ መስጫ ወረቀት ያዘጋጃል፡፡

2. ቦርዱ የሚያዘጋጀው የድምጽ መስጫ ወረቀት የእጩዎች ፎቶግራፍ፣ የእጩ መለያ ምልክት፣ የእጩዎች ሙሉ ስምና የፖለቲካ ፓርቲያቸው መጠሪያን አካቶ ሊይዝ ይገባል፡፡

3. ቦርዱ በየምርጫ ጣቢያው በተመዘገበው መራጭ ቁጥር ልክ የሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከጥቂት መጠባበቂያ ጋር ይልካል፡፡

4. ቦርዱ እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

5. ማንኛውም የምርጫ ሰነድ ከአንድ ሰው ወደ ሌላ በሚተላለፍበት ጊዜ ሕጋዊ የርክክብ ስርዓትን ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡ዝርዝሩ በቦርዱ መመሪያ ይወሰናል

## <u>ምዕራፍ አምስት</u>
## <u>የድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ</u>

### 57. የቆጠራ ቦታ

1. የማንኛውም ምርጫ ድምፅ ቆጠራ የሚካሄደው ድምፅ በተሰጠበት ምርጫ ጣቢያ ነው፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጸጥታ መደፍረስ ወይም ተመሳሳይ አስገዳጅ ምክንያት የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚ ለምርጫ ክልሉ ጥያቄ አቅርቦ ሲፈቀድ ወይም የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ሲወስን የድምጽ ቆጠራው በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ይካሄዳል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የሚካሄደው ቆጠራ የምርጫ ጣቢያው የእጩ ወኪሎች፣ ከህዝብ የተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ታዛቢዎች በተገኙበት ይደረጋል፡፡

4. የዚህ አንቀፅ አፈፃፀም ዝርዝርን ቦርዱ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

### 58. የድምጽ ቆጠራ አጀማመርና ሂደት

1. ድምፅ አሰጣጡ እንደተጠናቀቀ የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ቆጠራ ለመጀመር የእጩ ወኪሎች፣ ከህዝብ የተመረጡ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት እና የምርጫ ታዛቢዎች እንዲገኙ በማድረግ፦

   ሀ. በዕለቱ ድምፅ የሰጡ መራጮችን ብዛት ይመዘግባል፣

   ለ. የተበላሹና ሥራ ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት ይመዘግባል፡፡

2. ድምፅ ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት የድምፅ መስጫው ሳጥን እሽጉ ያልተከፈተ እና ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ በፊት በታሸገበት ሁኔታ መቆየቱን፣ የድምጽ ሳጥኑም ያልተቀደደ፣ ያልተሰበረ ወይም ብልሽት ያልደረሰበት መሆኑን ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት አካላት ካረጋገጡ እና ቃለጉባኤ ከተያዘ በኋላ እሽጉን በመክፈት ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች በሙሉ ይወጣሉ፡፡ የድምጽ መስጫ ሳጥኑም ባዶ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

3. ምርጫው የተካሄደው ለተለያዩ ምክር ቤቶች ከሆነ በመጀመርያ ለየምክር ቤቱ የተሰጡት የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከተለዩ በኋላ የአንዱ ምክር ቤት ተቆጥሮ እና ለእያንዳንዱ እጩ የተሰጠው የድምጽ ቁጥር ተመዝግቦ እንዳለቀ የሌላው ምክር ቤት ቆጠራ በተመሳሳይ ይካሄዳል፡፡

4. በድምፅ ቆጠራው ሂደት ግድፈት አለ በማለት አንድ የምርጫ አስፈፃሚ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወኪል ቅሬታ ያቀረበ እንደሆነ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ

ኮሚቴ ጉዳዩን መርምሮ ወዲያውኑ ወይም ቢዘገይ ከ12 ሰዓት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል። በምርጫ ጣቢያው ወይም በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የድምጽ ቆጠራው ሁኔታዎች እስኪጣሩ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ ዳግም ቆጠራ እንዲካሄድ ሊደረግ ይችላል።

## 59. ስለ ዋጋ አልባ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች

1. ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ዋጋ አልባ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

    ሀ. የመራጩ ማንነት በስም የተገለፀበት ከሆነ፣

    ለ. ለም/ቤቱ ሊመረጥ ከሚቻለው ተመራጮች ቁጥር በላይ ላላቸው እጩዎች ምልክት የተደረገበት ከሆነ፣

    ሐ. ምንም ምልክት ያልተደረገበት ከሆነ፣

    መ. መራጩ ማንን እንደመረጠ መለየት የሚያስቸግር ከሆነ፣

    ሠ. ሕጋዊ የድምፅ መስጫ ወረቀት ያልሆነ ወይም በምርጫ ጣቢያው ያልተሰራጨ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሆነ፣

2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 መሠረት ዋጋ አልባ የተደረጉ ወረቀቶች በጀርባቸው "ውድቅ" የሚል በጉልህ ተፅፎባቸው ለብቻቸው ተቆጥረው ይታሸጋሉ።

## 60. ስለድምፅ ቆጠራ መጠናቀቅ

በምርጫ ጣቢያ የሚካሄደው የድምጽ ቆጠራ እንደተጠናቀቀ፡-

1. በወቅቱ በቦታው የተገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች፤ እና የእጩ ወኪሎች አጠቃላይ የድምፅ አሰጣጥ እና የቆጠራው ሂደት እንዲሁም ውጤቱ ትክክል ስለመሆኑ ለዚሁ ዓላማ በሚዘጋጀው ቃለ ጉባኤ እና የምርጫ ጣቢያ ውጤት መተማመኛ ቅፅ ላይ ይፈራረማሉ። ሆኖም በሂደቱና በውጤቱ ቅሬታ ያለው የእጩ ወኪል ቅሬታውን አስመዝግቦ ይፈርማል።

2. የተቆጠረው የድምፅ መስጫ ወረቀት ታሽጐ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የተፈረመው የምርጫ ጣቢያ ውጤት መተማመኛ ቅፅ፣ ቃለጉባዔ እና የምርጫ ውጤት ማሳወቂያ ቅፅ ለምርጫ ክልሉ ወዲያውኑ ይላካል።

3. የድምፅ ቆጠራ ውጤት መተማመኛውን ለፈረመው የእጩ ወኪል አንድ ቅጂ ወዲያውኑ ይሰጣል።

## 61. የቆጠራ ውጤት አገላለፅ

1. በምርጫ ጣቢያ የተደረገ የቆጠራ ውጤት በጣቢያው የተመዘገቡና ድምጽ የሰጡ መራጮችን ብዛት፣ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ያልዋሉና ከጥቅም ውጭ የሆኑ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን ብዛት እና እያንዳንዱ እጩ ያገኘውን የድምጽ ብዛት በመለየት ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያው ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወጥቶ ለህዝብ በይፋ ይገለፃል፡፡

2. የምርጫ ክልል የምርጫ ጽህፈት ቤቶች የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ውጤት ከየምርጫ ጣቢያው እንደደረሳቸው ወይም የተረጋገጠ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር በምርጫ ክልሉ የድምጽ መስጫ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ከ አምስት ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት ደምረው የተገኘውን ውጤት ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ፡፡

3. እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምጽ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ተለይተው ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ምርጫ እንዲሰጥባቸው ይደረጋል፡፡

4. የምርጫ ክልል የምርጫ ኃላፊዎች ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይፋ ያደረጉትን ውጤት፡-

   ሀ. ለተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው የውጤት መተማመኛ ይሰጣሉ፣

   ለ. በውጤት ማሳወቂያ ቅፅ ሞልተው አንድ ቅጂ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት፥ እንዲሁም ሌሎች ቅጂዎች በየደረጃው ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይልካሉ፡፡

5. ቦርዱ በአጠቃላይ የምርጫ ውጤት ከየምርጫ ክልሉ ተጠናቆ እስኪደርሰው ድረስ ከየምርጫ ክልሉ የመጣለትን የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት የምርጫ ውጤት በጊዜያዊነት በቦርዱ ጽህፈት ቤት ሊገልጽ ይችላል፡፡ ሆኖም የምርጫው ይፋዊ ውጤት በ10 ቀናት ውስጥ ካልተገለጸ ቦርዱ ጊዜያዊ ውጤቱን ይፋ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

6. በምርጫ ክልሎች የተሰበሰቡ ድምጽ የተሰጣባቸው ወረቀቶች ታሽገው ከምርጫ ክልሉ በቅርበት በሚገኝ የቦርዱ እርከን ጽህፈት ቤት ወይም በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡ ድምጽ የተሰጠባቸው ወረቀቶችን አያያዝ እንዲሁም አወጋገድ አስመልክቶ ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 62. ይፋዊ መግለጫ

1. የምርጫው ሂደት ከተጠናቀቀና አስፈላጊ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ የተረጋገጠ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ከምርጫው ቀን ቀጥሎ ባሉት 10 ቀናት ውስጥ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች የያዘ ይፋዊ መግለጫ ያወጣል፡፡

   ሀ. የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር ፣

   ለ. ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር፣

   ሐ. ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ የተመዘገቡ መራጮች መጠን በመቶኛ፣

   መ. የተመረጡ እጩዎች የስም ዝርዝርና የተመረጡበት የምርጫ ክልል፣

   ሠ. የአሸናፊ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲሁም የግል ተወዳዳሪዎች ስምና ለየምክር ቤቱ ያሸነፉትን መቀመጫ ብዛት፣

   ረ. ጥቅም ላይ የዋለ፣ ያልዋለ፣ ከጥቅም ውጭ የሆነ የድምፅ መስጫ ወረቀት እያንዳንዱ እጩ በየምርጫ ጣቢያው ያገኘው የድምፅ ውጤት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች ፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ክልል ደረጃ በተገለጹ ውጤቶች ላይ የቀረቡ አቤቱታዎች ውጤት መግለጹን እንዲዘገይ የግድ የሚሉ ከሆነ ይፋዊ ውጤት የሚገለጽበት ጊዜ እስከ 20 ቀን ድረስ ሊዘገይ ይችላል፡፡

# ክፍል አራት
# ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች በጠቅላላ
## ምዕራፍ አንድ
## የፖለቲካ ፓርቲ አመሰራረት

## 63. የፖለቲካ ፓርቲ ስለ መመስረት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው::

2. ማንኛውም እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በዚህ አዋጅ መሠረት የአገር አቀፍ ወይም የክልል የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው፡፡
3. ከላይ በንዑስ ቁጥር (1) እና (2) የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ አይችሉም፤

   ሀ/ ዳኛ፣

ለ/ የመከላከያ ሰራዊት አባል፣

ሐ/ የፖሊስ የደህንነት እና የጸጥታ አካላት ሰራተኛ፣

መ/ የቦርዱ ባለስልጣናት እና ሰራተኞች።

4. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (3) የተጠቀሱት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ ከፈለጉ የመንግሥት ስራቸውን መልቀቅ አለባቸው።

5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገውን የጣሰ ሰው ከያዘው የመንግሥት ሥራ በራሱ ፈቃድ እንደለቀቀ ይቆጠራል።

6. በፍርድ ቤት ወሳኔ የመምረጥና የመመረጥ መብቱ የታገደበት ሰው እገዳው በሚቆይበት ዘመን የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አይችልም።

## 64. አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው፤

ሀ. 10 000 መሥራች አባላት ሲኖሩት፣

ለ. ከመስራች አባላቱ ውስጥ ከአርባ በመቶ የማይበልጡት የአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ፣

ሐ. የተቀሩት መሥራች አባላት ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ ከሚገኙት ሌሎች ክልሎች ውስጥ ቢያንስ በአራቱ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑና፣

መ. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 /ሐ/ መሠረት ከየክልሉ ለሀገር አቀፍ ፓርቲ መሥራችነት ከሚመዘገቡት አባላት በእያንዳንዱ ክልል አሥራ አምስት በመቶው መደበኛ ነዋሪ ሲሆኑ ነው።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተጠቀሱት መስራች አባላት እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በላይ ሆኖ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ፣ የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆን መስማማታቸው ከሙሉ ስማቸው ጎን ባኖሩት ፊርማቸው የገለፁና በተመዘገቡበት አካባቢ ነዋሪ ስለመሆናቸው ለፓርቲው ማረጋገጫ ያቀረቡ መሆን አለባቸው።

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (2) ሥር የተመለከተው የመሥራች አባላት መረጃ የአባሉን ሙሉ ስም፤ ጾታ፣ እድሜ፣ ቀበሌ ወይም ወረዳ፤ እንደየአግባብነቱ የሚኖሩበትን ቦታ ልዩ ስም ወይም የቤት ቁጥር፣ የነዋሪነት ማረጋገጫ አይነት፣ ያቀረበው የነዋሪነት ማረጋገጫ

መለያ ቁጥር ያለው ከሆነ መለያ ቁጥሩ፤ ፊርማ እና የምዝገባ ቀን የሚገልጽና እንዲሁም የመረጃ ሰብሳቢውን ስምና ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡

4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተመለከተው መሠረት ፓርቲው የሚያቀርበው የመስራች አባላት መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ፓርቲው ወይም ፓርቲውን ለማስመዝገብ የሚያመለከተው ሰው ቃለ መሃላ ያቀርባል፡፡ አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም ቦርዱ መስራች አባላቱ በሚኖሩበት አካባቢ የነዋሪነት ማረጋገጫ የመስጠት ስልጣን ካለው አካል ጋር በመተባበር ሊያጣራ ይችላል፡፡

5. በአባልነት ያልተመዘገበ ሰውን የተመዘገበ በማስመሰል፣ ሐሰተኛ ስምና ፊርማ በማዘጋጀት፣ የሌለን ሰው እንዳለ በማስመሰል ወይም በሌላ የተጭበረበረ መንገድ የቀረበ መረጃ በማናቸውም ሰው በሚቀርብ ጥቆማ ወይም ቦርዱ በራሱ በሚያደርገው ማጣራት የተደረሰበት እንደሆነ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ መሠረት የሚወሰደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ፤

ሀ) ከላይ የተጠቀሰው የማጭበርበር ተግባር የታወቀው ፓርቲው በምዝገባ ላይ እያለ ከሆነ ያቀረበው የምዝገባ ማመልከቻ ውድቅ ተደርጎ ለሚቀጥሉት ሦስት አመታት ፓርቲው በፖለቲካ ፓርቲነት ከመመዝገብ ይከለከላል፤ እንዲሁም ከማጭበርበር ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም የፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ እና ግለሰብ በፓርቲ መሪነት ወይም አባልነት ከመሳተፍ ይታገዳል፡፡

ለ) ከላይ የተጠቀሰው የማጭበርበር ተግባር የታወቀው ፓርቲው ተመዝግቦ ፈቃድ ከተሰጠው በኋላ ከሆነ የተሰጠው ፈቃድ ተሰርዞ ለሚቀጥሉት ሦስት አመታት ፓርቲው በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ እንዲሁም ከማጭበርበር ተግባሩ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛው የፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ እና ግለሰብ በፓርቲ መሪነት ወይም አባልነት መሳትፍ እንዳይችል ይደረጋል፡፡

6/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው መስራች አባላትን በሚያሰባስብበት ጊዜ የጾታን እና የተለያዩ በአከባቢው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተዋጽኦ ባገናዘበ መልክ መሆን አለበት፡፡

7/ ቦርዱ አንድ የተመዘገበ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ዝቅተኛውን የአባላት ቁጥር ያሟላ መሆኑን ፓርቲው በየሁለት አመቱ የሚያቀርበውን የአባላት ዝርዝር ሪፖርት መሠረት በማድረግ ያረጋግጣል ፡፡

8/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት መስራች አባላት የፈረሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው፡፡

9/ በማናቸውም ደረጃ ምርጫ በሚካሄድበት ዘመን የሚቀርብ የምዝገባ ጥያቄ የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ90 ቀናት በፊት የቀረበ ከሆነ የእጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩ በፊት መጠናቀቅ አለበት፡፡

## 65. የክልል የፖለቲካ ፓርቲ ስለ መመስረት

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በክልል የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው፤

   ሀ/ 4000 መስራች አባላት ሲኖሩት፤ እና

   ለ/ ከነዚህ መስራች አባላት ውስጥ ከስልሳ በመቶ በላይ የሆኑት የክልሉ መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ ነው።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተጠቀሱት መስራች አባላት እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ፣ የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን የገለፁና በተመዘገቡበት አከባቢ ነዋሪ ስለመሆናቸው ለፓርቲው ማረጋገጫ ያቀረቡ መሆን አለባቸው።

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተመለከተው የመስራች አባላት መረጃ የአባሉን ሙሉ ስም፤ ጾታ፣ እድሜ፣ ቀበሌ ወይም ወረዳ፤ እንደየአግባብነቱ የሚኖሩበትን ቦታ ልዩ ስም ወይም የቤት ቁጥር፣ የነዋሪነት ማረጋገጫ አይነት፣ ያቀረበው የነዋሪነት ማረጋገጫ መለያ ቁጥር ያለው ከሆነ መለያ ቁጥሩ፤ ፊርማ እና የምዝገባ ቀን የሚገልጽና እንዲሁም የመረጃ ሰብሳቢውን ስምና ፊርማ የያዘ መሆን አለበት።

4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) በተመለከተው መሠረት ፓርቲው ያቀረበው የመስራች አባላት መረጃ የሚረጋገጥበት መንገድ እንዲሁም የተጭበረበረ መረጃ ከተገኘ የሚወሰደው እርምጃ ከላይ በአንቀጽ 64(4) እና (5) በተቀመጠው መሠረት ይሆናል።

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው መስራች አባላትን በሚያሰባስብበት ጊዜ የጾታን እና የተለያዩ በአከባቢው ያሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ተዋጽኦ ባገናዘበ መልክ መሆን አለበት።

6. ቦርዱ አንድ የተመዘገበ አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር ያሟላ መሆኑን ፓርቲው በየሁለት ዓመቱ በሚያቀርበው የአባላት ዝርዝር ሪፖርት መሠረት ያረጋግጣል።

7. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት መስራች አባላት የፈርሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው።

8. በማናቸውም ደረጃ ምርጫ በሚካሄድበት ዘመን የሚቀርብ የምዝገባ ጥያቄ የመራጮች ምዝገባ ከመጀመሩ ከ90 በፊት የቀረበ ከሆነ የእጩዎች ምዝገባ ከመጀመሩና የምርጫ ዘመቻ የጊዜ ሰሌዳ ከመውጣቱ በፊት መጠናቀቅ አለበት።

9. ቦርዱ በአንቀጽ 64 እና በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ተግባራት አፈጻጸም በሚያወጣው መመርያ ይወስናል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ

### 66. ስለምዝገባ

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ በፖለቲካ ፓርቲነት ለመንቀሳቀስ የሚችለው በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርዱ ተመዝግቦ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በስሙ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፣ የንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ መሆን፣ መሸጥ፣ መለወጥ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ንብረት ማስተላለፍ ወይም ዓላማውን ተከትሎ ማናቸውንም ሕጋዊ ተግባሮች ማከናወን ይችላል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የፓለቲካ ፓርቲ ለማቋቋም የሚፈልጉ የዜጎች ስብስብ ለቦርዱ ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ እንዲሰጣቸው ማመልከት ይችላሉ፡፡

4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ፤ በጽሑፍ የሚቀርብ የምዝገባ ጥያቄ፣ለአገር አቀፍ ፓርቲነት ቢያንስ 200 ፣ ለክልል ፓርቲነት ቢያንስ 100 አመልካቾች የፈረሙበት የስብሰባ ቃለ ጉባኤ፣ የሚመሰረተው የፓለቲካ ፓርቲ ጊዜያዊ ስም፣ የምርጫ ህጉንና ተያያዥ ህጎችን የሚያከብሩ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ እና ቦርዱ የሚወስነውን የአገልግሎት ክፍያ መፈጸማቸውን የሚገልጥ ማስረጃ ማካተት አለበት፡፡

5. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሱት ሰነዶች መሟላታቸውን ካረጋገጠ በኋላ ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ የሚያገለግለው ለሦስት ወራት ብቻ ነው፡፡ ሆኖም አመልካቾች በቂ ምክንያት ያቀረቡ እንደሆነ ጊዜያዊ ፈቃዱ ለተጨማሪ ሦስት ወራት ሊራዘም ይችላል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ መሠረት ጊዜያዊ የምዝገባ ፈቃድ ያገኘ የፓለቲካ ፓርቲ፤ ጊዜያዊ ፈቃዱን መጠቀም የሚችለው በዚህ አዋጅ መሠረት ፓርቲውን ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ ተግባራትን ለማከናወን ብቻ ይሆናል፡፡

### 67. በፓርቲነት ለመመዝገብ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የምዝገባ ማመልከቻ በፖለቲካ ፓርቲው መሪ ተፈርሞ ለቦርዱ መቅረብ አለበት፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 72 መሠረት የተዘጋጀ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ፅሁፍ፣

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 73 መሠረት የተዘጋጀ የፖለቲካ ፓርቲው ፕሮግራም፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 74 መሠረት የተዘጋጀ የፖለቲካ ፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ፣

መ/ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በኃላፊነት ለመስራት መስማማታቸውን የሚያስረዳ በፊርማቸው የተረጋገጠ ሰነድ፣

ሠ/ መስራቾች የፈረሙበትና ለሕዝብ በይፋ የሚገለጽ ሰነድ፣

ረ/ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ነጻና ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ የተመረጡ መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ፣

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /2/ የተዘረዘሩት ሰነዶች አምስት አምስት ቅጂ ከምዝገባ ማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት።

4. የምዝገባ ጥያቄ ማመልከቻ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ፦

ሀ/ የምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ እና

ለ/ በየጊዜው ለሚደረጉ የመሠረታዊ ሰነዶች ማሻሻያ አገልግሎት ክፍያ ይከፍላል።

5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /4/ /ሀ/ የተደነገገውን ክፍያ የከፈለበት ደረሰኝ ከምዝገባ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት።

6. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /4/ የተደነገገው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በቦርዱ ይወሰናል።

7. በዚህ ህግ መሠረት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች ለሕዝብ ግልፅ መሆን አለባቸው።

68. **የቦርዱ ኃላፊነት**

1. ቦርዱ በአንቀጽ 67 መሠረት የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ በ21 ቀናት ውስጥ ከመረመረ በኋላ አመልካቹ የፖለቲካ ፓርቲው ማሟላት ያለበትን ሁሉ ያላሟላ እንደሆነ ይህንኑ በ 30 ቀናት ውስጥ እንዲያሟላ በጽሑፍ ያሳውቀዋል፡፡

2 ቦርዱ በንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት በሚያደርገው ምርመራ ማመልከቻው የተሟላ ሆኖ ካገኘው በ15 ቀናት ውስጥ አግባብነት ባለው የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም በድረ ገጹ እና በሶሻል ሚዲያ ገጾቹ በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ማመልከቻ ባቀረበው ፓርቲ ስም፣ አርማ ወይም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተቃውሞ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞውን እንዲያቀርብ በመጋበዝ ለህዝብ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

3. በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ14 ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡ ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ ፈቃድ አይሰጥም፡፡

4. ቦርዱ ለምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ተያያዥ መረጃዎች ወይም ማብራሪያ እንዲቀርብለት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

5. ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 67 መሠረት የሚቀርብለትን ማመልከቻና አባሪ ሰነዶች ተቀብሎ በመመርመር ሰነዶቹ በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት የተሟሉ እና ትክክለኛ መሆናቸውን አረጋግጦ፣ ፓርቲው ህገመንግስቱን፣ ይህንን አዋጅ፣ ሌሎች ተዛማጅ ሕጎችንና የሥነ ምግባር ደንቦችን የሚያከብር መሆኑን ማረጋገጫ እንዲሰጥ በማድረግ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲውን ዋና ጽሕፈት ቤት በመጎብኘት የምዝገባ ማመልከቻውን በተቀበለ በ45 ቀናት ጊዜ ውስጥ የምዝገባውን ሥርዓት አጠናቅቆ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል፡፡

6. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት የተመዘገበን የፖለቲካ ፓርቲ አግባብ ሆኖ ባገኘው የብዙኃን መገናኛ ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

7. ቦርዱ በዚህ ክፍል ምዕራፍ ሰባት መሠረት የፖለቲካ ፓርቲን የገቢ ምንጭ የወጪ ዝርዝር እና ንብረት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህገ ወጥ ድርጊት ተፈጽሞ ሲያገኝም በዚህ አዋጅ መሠረት ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፡፡

8. ቦርዱ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 100 መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የተደረገ ድጋፍና የድጋፉ አጠቃቀም ዝርዝር፤እና

ለ/ ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወቅታዊ እና ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

9/ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 105 በተደነገገው መሠረት የኦዲት ሪፖርት እንደደረሰው ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም እንዲመረመር ሊያዝ ይችላል፡፡

## 69. መመዝገብ ስለማይችል የፖለቲካ ፓርቲ

1 ለመመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበው የፖለቲካ ፓርቲ፡

ሀ) የመረጠው ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ ወይም የመለያ ምልክት ከአገሪቱ ባህልና የስነ ምግባር እሴቶች አኳያ ተቀባይነት የሌለው ከሆነ፣ወይም

ለ) የመረጠው ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ ወይም የመለያ ምልክት በሌላ ፓርቲ የተያዘ ከሆነ ወይም ከሌላ ፓርቲ ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ ወይም የመለያ ምልክት ጋር መራጮችን ሊያሳስት በሚችል ደረጃ የሚቀራረብ ከሆነ፣ ወይም

ሐ) የመረጠው ስም፣ አሕጽሮተ ስም፣ አርማ፣ የመለያ ምልክት፣ የመመስረቻ ጽሑፍ ወይም የመተዳደሪያ ደንብ በዘር፣ በኃይማኖት እና በመሳሰሉት ልዩነቶች ላይ የተመሰረተ ጥላቻና ጠላትነት በዜጎች፣ በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና በሕዝቦች መካከል በማስፋፋት ጦርነትና ግጭት መፍጠርን ዓላማ ያደረገ ወይም ሰዎችን በዘር፣ በኃይማኖት ወይም በማንነት ላይ ተመስረቶ ከአባልነት ወይም ከደጋፊነት የሚያገል ከሆነ፤ ወይም

መ) የፖለቲካ ዓላማውን በትጥቅ ለማራመድ የተደራጀ ከሆነ፣ ወይም

ሰ) የውጭ ሀገር ዜጎች አባል የሆኑበት የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ፣ ወይም

ረ) ሕገወጥ ዓላማ ለማካሄድ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ፣
ቦርዱ አይመዘግበውም፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔው በጽሑፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ አቤቱታ ያቀረበው አካል ለዚህ ጉዳይ አፈፃፀም ሕጋዊ ሰውነት እንዳለው ተቆጥሮ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ተመርጦ በምዝገባ ማመልከቻው ላይ ፊርሞ ያቀረበው የፓርቲው መሪ የፓርቲው ሕጋዊ ወኪል እንደሆነ ይቆጠራል፡

## 70. በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ስለማይችል ድርጅት ወይም ማህበር

የሚከተሉት ድርጅቶት ወይም ማህበራት በዚህ አዋጅ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገቡ አይችሉም፣

1/ በንግድ ሕግ ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት፣ የንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎችን ለማከናወን የተቋቋሙ ማሕበሮች ወይም ድርጅቶች፣

2/ ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ ወይም ለበጎ አድራጎት ተግባር የተቋቋሙ ማሕበራት ወይም ድርጅቶች፣

3/ የብዙኃን መገናኛ ፣ የሠራተኛ እና የሙያ ማሕበራት፣

4/ የመረዳጃ ማሕበራት፣

5/ የሃይማኖት ድርጅቶች፣

6/ ዕድርና ዕቁብን የመሳሰሉ ማሕበራዊ ተቋሞች።

## ምዕራፍ ሶስት
## የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች

### 71. የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉት ዋና ዋና ሰነዶች ይኖሩታል፤

ሀ. የመመስረቻ ፅሁፍ፣

ለ. የፖለቲካ ፕሮግራም፣

ሐ. የመተዳደሪያ ደንብ፣

መ የሃብትና ንብረት፣ የገቢና የወጪ ሰነዶች፣

2. በንኡስ አንቀጽ 1 ከ(ሀ) እስከ (ሐ) የተጠቀሱትን ሰነዶች ለማሻሻል የፈለገ የፖለቲካ ፓርቲ አስቀድሞ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት። ቦርዱ የቀረበለትን የማሻሻያ ጥያቄ ተቀብሎ እንደ አግባብነቱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68 ድንጋጌዎች መሠረት ያስተናግዳል።

### 72. ፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ፅሁፍ

1/ የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት የሚፈልጉ ግለሰቦች መስራች ሆነው ለማደራጀት የፈለጉትን የፖለቲካ ፖርቲ ማቋቋማቸውን የሚገልጹበት የመመስረቻ ጽሑፍ ይኖራቸዋል።

2/ የመመስረቻ ጽሑፉ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ ይሆናል፤

ሀ/ የፓርቲው መጠሪያ ሙሉ ስም እና አህፅሮተ ስም፣

ለ/ የፓርቲው ዓርማ፣

ሐ/ የፓርቲው ዓላማ፣

መ/ የፓርቲው ንብረትና የገቢ ምንጭ፣

ሠ/ ፓርቲው የተመሰረተበት ቀን እና ዓመተ ምህረት

ረ/ የፓርቲው ዋና መሥሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች አድራሻ፣

ሰ/ የመተዳደሪያ ደንቡ አወጣጥ ሥርዓት፣

3/ የፓርቲው የመመስረቻ ጽሑፍ በመስራች ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መሆን አለበት፡፡

## 73. የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማው አድርጎ የያዘውን የፖለቲካ እምነት የሚቀርጽበት በፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ የሚጸድቅና የሚሻሻል የፖለቲካ ፕሮግራም ይኖረዋል፡፡

## 74. የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡም የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ/ የአባላት ቅበላና ስንብት ሁኔታ፤

ለ/ የአባላቱ መብትና ግዴታ፣

ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲው ልዩ ልዩ አካላት፣ የሚመረጡበት ሥርዓት፣የአገልግሎት ዘመን እና የስራ ኃላፊነታቸውን፣

መ/ የአባልነት መዋጮ አይነትና አከፋፈል እንዲሁም አባላቱ በፓርቲው ሥራ ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ፣

ሠ/ የፓርቲው የስብሰባ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት፣

ረ/ በአባላቱ ላይ ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓት እና የሥነ ምግባር እርምጃ፣

ሰ/ የጠቅላላ ጉባኤ አባላትን ቁጥር ቢያንስ በዚህ አዋጅ መሠረት ፓርቲ ለመመስረት ከተቀመጠው ከዝቅተኛው የመስራች አባላት ቁጥር 5 በመቶ በማድረግ የሚወስን ድንጋጌ

ሸ/ የፖለቲካ ፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ቢያንስ በሦስት አመት አንድ ጊዜ መካሄድ ያለበት መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ ፣

ቀ/ የፓርቲው ቅርንጫፎች አወቃቀርና አሠራርን ጨምሮ የፓርቲውን መዋቅራዊ አደረጃጀትና የስልጣን ተዋረድ፣

በ/ የፓርቲውን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮችን ዝርዝር፣

ተ/ የፖለቲካ ፓርቲው ከሌላ ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች ጋር ውህደት፣ ቅንጅት ወይም ግንባር የሚፈጥርበት፥ እንዲሁም ፓርቲው የሚፈርስበትን የውሳኔና የድርጊት ሂደቶች፣

ቸ/ የፓርቲው አባላት ለአገር አቀፍና በየደረጃው ላሉ አገራዊ ምርጫዎች የሚታጩበት ሥርዓት፣

ኀ/ የፖለቲካ ፓርቲው የሰው ኃብት፣ የፋይናንስ እና የኦዲት አስተዳደር ስርአት አሰራር፣

ነ/ የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር ስርአት፣ ፣ የገቢ ማስገኛ አሰራር እና በነዚህ ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ስልጣን ያለውን አካል ወይም ኃላፊን የሚገልጽ ድንጋጌ ፣

ኘ/ የፖለቲካ ፓርቲው የወስጥ አለመግባባቶች አፈታት ሥርዓት፣

አ/ ማንኛውም አባል እኩል ድምፅ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ድንጋጌ፤

2. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የፖለቲካ ፓርቲው አባል በዜግነቱ የተረጋገጠለትን መብት የሚቀንስ ወይም የተጣለበትን ግዴታ የሚሽር ሊሆን አይችልም።

3. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የፓርቲው አመራሮችና በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች አመራረጥ ግልጽ፥ ነጻና ፍትሃዊ እንዲሁም በሚስጥር በሚሰጥ ድምጽ መንገድ የሚመረጡ መሆናቸውን መደንገግ አለበት።

4. በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ለኃላፊነት ቦታ የሚደረጉ ምርጫዎች የጾታ ተዋጽኦን ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል።

5. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን አዋጅ አንቀጽ 75 እና ከአንቀጽ 86 እስከ አንቀፅ 90 የተደነገጉትን ያገናዘበ መሆን አለበት።

6. በፖለቲካ ፓርቲ አባላት መሀከል የፓርቲውን ሕገ ደንብ አፈፃፀም እና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች አለመግባባት ተፈጥሮ ለቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብ ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለቦርዱ የሚያቀርብ የባለሞያዎች ጉባኤ ቦርዱ ያቋቁማል፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የፖለቲካ ፓርቲ መብት እና ግዴታ

### 75. የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ጉዳይ ላይ ስላለው ነፃነት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1/ የፖለቲካ ፕሮግራሙንና የመተዳደሪያ ደንቡን የሚያፀድቅበትንና የሚያሻሽልበትን እንዲሁም ስብሰባ የሚያካሂድበትን ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል፡፡

2/ በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት የፖለቲካ ሥራውን የሚመሩ፣ ውሣኔ የሚሰጡ እና የሚያስፈፅሙ የአመራር አካላት ይኖሩታል፡፡

### 76. ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ስለማቋቋም

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ሥራውን ለማካሄድ በሀገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡

2/ በአገር አቀፍ ደረጃ፣ በክልልና ከክልል በታች ቅርንጫፎች ያሉት የፖለቲካ ፓርቲ በቅርንጫፎቹ መካከል ያለውን ግንኙነትና የስልጣን ተዋረድ በመተዳደርያ ደንቡ መደንገግ አለበት፡፡

### 77. ከገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ በሚገኘው ገቢ ላይ ምንም ዓይነት የገቢ ግብር አይከፍልም፡፡

2/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በሕግ በተወሰነው መሠረት የገቢ ግብር ሰብስቦ ለመንግሥት ገቢ ከማድረግ ነፃ ነው፡፡

### 78. ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

1/ ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ/ የአባላቱን ብዛት፣ የጾታ ስብጥር፣ የእድሜ ሁኔታ እና የመኖርያ ቦታ የሚያሳይ አመታዊ ሪፓርት የማቅረብ፥

ለ/ ቦርዱ ሲጠይቅ በሕጉ መሠረት የሚፈለገው ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መስፈርቶች ተሟልተው መገኘታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ የማቅረብ፣

ሐ/ ግንባር ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም ለመቀናጀት የሚደረጉ ስብሰባዎች ሲኖሩ ቦርዱ በስብሰባው ላይ እንዲገኝ ቢያንስ ከ30 ቀናት በፊት የማሳወቅ፣

መ/ በዚህ አዋጅ መሠረት በየዓመቱ ወይም ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ፓርቲው እንደየአግባብነቱ በኦዲተር ወይም በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ የሃብትና ዕዳ መግለጫ በፓርቲው መሪ ፊርማ ለቦርዱ የጽሑፍ ሪፖርት የማቅረብ፣

ሠ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1 /መ/ የተጠቀሰው ሪፖርት የፖለቲካ ፓርቲውን የገቢ ወይም የሃብቱን ምንጭ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

2/ ቦርዱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገውን ግዴታ በማያሟላ የፖለቲካ ፓርቲ ላይ የአንድ ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኂላ በአንቀፅ 98 መሠረት አስፈላጊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

3/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው መሪ በዚህ አንቀፅ መሠረት ለቦርዱ በጽሑፍ ያሳወቀው የሃብትና ዕዳ መግለጫ ሐሰተኛ ሆኖ ከተገኘ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 98 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ሕግ ይጠየቃል፡፡

4/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 68 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገውን መረጃ ወይም ማብራሪያ ሳይሰጥ የቀረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 98 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

5/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 76 መሠረት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ያቋቋመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን አድራሻ እና የመሥሪያ ቤቱን ኃላፊዎች ወይም ተወካዮች ቅርንጫፉን ባቋቋመ በአንድ ወር ውስጥ ለቦርዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 79. መረጃ የመስጠት ግዴታ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ የተዘረዘሩ መረጃዎች እንዲያቀርብ በቦርዱ ሲጠየቅ በሰነድ የተረጋገጠ የጽሑፍ መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ የሚካሄድ ሲሆን የቦርዱ ተወካይ በስብሰባው ላይ እንዲገኝ 30 ቀናት አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የተጠየቀውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም የሰጠው መረጃ ሃሰት መሆኑን እያወቀ የሰጠ እንደሆነ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 98 /1/ /መ/ በተደነገገው መሠረት እርምጃ ይወስዳል፡፡

## 80. የአመራር አባላትን ስለማሳወቅ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አዲስ አመራር አባላትን የመረጠ እንደሆነ ይህንኑ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በተለያየ ምክንያት የአመራር አባላቱ የተጓደሉና ቁጥራቸውም ከ50%+1 በታች ከሆነ በ30 ቀናት ውስጥ ምርጫ በማካሄድ ማሟላት አለበት፣ ይህንንም ክንውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 81. የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች አጠባበቅ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ ስምንት ንዑስ ክፍል ሁለት የተመለከቱትን የሂሣብ መዝገብ፣ የስጦታ ሰርተፊኬት፣ የባለንብረትነት ማረጋገጫ ሰነዶችን በሚገባ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

2/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገው ቢኖርም በቦታው መጣበብና በሠራተኛ እጥረት ምክንያት ከ10 ዓመት ዕድሜ በላይ ያስቆጠሩ የሂሣብ ሰነዶች ማስወገድ ይችላል፡፡

3/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ እና /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፓርቲውን ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ጠብቆ መያዝ አለበት፡፡

## 82. ስለፖለቲካ ፓርቲ ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢ፣ የወጪ፣ የሃብትና የእዳ መዛግብቱንና ሰነዶቹን በአግባቡ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡ እነዚህ መዛግብት ሊይዟቸው የሚገቡ አርእስቶችና ዝርዝሮችን ቦርዱ በመመርያ ይወስናል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ በሚመለከተው ሕጋዊ አካል የተረጋገጠ የሙያ ብቃት ባለው የውጭ ኦዲተር ወይም ቃለ መሃላ በፈጸመ የሂሳብ ባለሙያ ወይም በቦርዱ በሚሾም ኦዲተር ሂሳቡን አስመርምሮ ለቦርዱ የኦዲት ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

3/ የሂሳብ ምርመራው ከሚካሄድበት የበጀት አመት በፊት በነበረው የበጀት አመት የሂሳብ እንቅስቃሴው ከብር 300000 (ሶስት መቶ ሺህ ብር) በታች የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ አመታዊ የሂሳብ ምርመራውን ቃለ መሃላ በፈጸመ የሂሳብ ባለሙያ አስመርምሮ ሪፖርቱን ለቦርዱ ያቀርባል።

4/ የሂሳብ ምርመራው ከሚካሄድበት የበጀት ዓመት በፊት በነበረው የበጀት ዓመት የሂሳብ እንቅስቃሴው ከብር 200000 (ሁለት መቶ ሺህ) በላይ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ ዓመታዊ የሂሳብ እንቅስቃሴውን በተመሰከረለት የወጭ ኦዲተር ወይም በቦርዱ በሚሾም ኦዲተር አስመርምሮ ሪፖርቱን ለቦርዱ ያቀርባል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ (2) እና ንዑስ (3) መሠረት የሚሾመው የውጪ ኦዲተር በፖለቲካ ፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ አካል ይሾማል።

6/ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር እንዲመረመሩ ሊጠይቅ ይችላል።

## 83. የኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ መብት

የፖለቲካ ፓርቲን ሂሳብ የሚመረምር ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ማንኛውንም ከፖለቲካ ፓርቲ ሀብትና ንብረት ጋር የተያያዘ ሰነድ እንዲቀርብለት የመጠየቅና የመመርመር መብት አለው።

## 84. ለፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር ሆኖ ሊሾም ወይም የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ ሊያገለግል ስለማይችል ሰው

ማንኛውም ሰው የፓርቲው ጠበቃ፣ ተቀጣሪ፣ የቦርድ አባል በመሆን አገልግሎ ወይም እያገለገለ ከሆነ ወይም በማንኛውም መልኩ የጥቅም ግጭት በሚያስከትል ደረጃ ከተመርማሪው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያለው ከሆነ የፖለቲካ ፓርቲው ኦዲተር ወይም የሂሳብ ባለሙያ ሆኖ ሊሰራ አይችልም።

## 85. በፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር አሰራር

1/ የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተርም ሆነ የሂሳብ ባለሙያ ወይም እንዲሁም እርሱ ቀጥሮ ያሰማራቸው ባለሞያዎች ስራቸውን በቅንነት፣ በታማኝነትና በገለልተኝነት ማከናወን አለባቸው።

2/ የኦዲተር የኦዲት ወይም የሂሳብ ባለሙያ የምርመራ ሪፖርት በጽሑፍ ሆኖ ለፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች መሰጠት አለበት።

3/ የፖለቲካ ፓርቲው ከሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ጋር የኦዲተሩ ወይም የሂሳብ ባለሙያው የሙያ ብቃት ሰርተፊኬት ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

## 86. የፖለቲካ ፓርቲ ስያሜና አርማ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚመርጠው ስያሜ ከተመሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲ ጋር የማይመሳሰል ወይም የማያደናግር የፓርቲው ብቸኛ መጠሪያ መሆን አለበት፡፡

2/ የፓርቲው ዓርማ እና ሰንደቅ ዓላማ፤

ሀ/ ከሌሎች ፓርቲዎች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ጋር የማይመሳሰል፣

ለ/ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል ጥላቻና ግጭትን የማይፈጥር፣

ሐ/ የጠረኝነት ወይም የሌላ ሕገወጥነት መልዕክት የማያስተላልፍ፣

መ/ ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወይም ዓርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፣

ሠ/ የሕዝብን ሞራል፣ ሥነ ምግባር እና የመሳሰሉትን የማይነካ መሆን አለበት፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብትና ግዴታ

## 87. በፖለቲካ ፓርቲ የመሳተፍ መብት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በፓርቲው ስብሰባዎች የመሳተፍ፣ ሐሳቡንና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፣ ድምፅ የመስጠት እና የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አለው፡፡

## 88. ስለአባልነት መዋጮ

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው በሚወስነው መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲው በየጊዜው የአባልነት መዋጮ ሊከፍል ይችላል፡፡

## 89. ከአባልነት ስለመወገድ

1/ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በሚወስነው መሠረት ከአባልነት ሊወገድ ይችላል፡፡

2/ ከፓርቲ አባልነት የተወገደ አባል በውሳኔው ላይ ቅሬታ ሲኖረው መወገዱ ከተገለጸት ወይም ውሳኔውን [ካወቀበት ቀን ጀምሮ] በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ስልጣን ላለው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም ለክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 90. ስለአባልነት

1/ የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መስራቾቹንና ከምስረታ በኋላ ፓርቲውን በአባልነት የተቀላቀሉትንም ሁሉ ያካተተ ነው፡፡

2/ የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ተላልፎ የማይሰጥ በአባሉ ብቻ ተወስኖ የሚቀር ነው፡፡

3/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በማንኛውም ጊዜ አባልነቱን ሊተው ይችላል፡፡

4/ የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን ምዕራፍ ድንጋጌዎች መቃረን የለበትም፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## ስለፖለቲካ ፓርቲዎች መዋሀድ፣ ግንባር መፍጠር፣ መቀናጀት እና መተካት

## 91. የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደት

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተዋህደው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ይችላሉ፡፡

2/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለመዋሃድ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን የጠቅላላ ምርጫ ወይም የአካባቢ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ከመውጣቱ ከሁለት ወራት በፊት በጽሑፍ ለቦርዱ ያቀርባሉ፤ ምዝገባውም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በቦርዱ ይፈፀማል፡፡

3/ ለውህደት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ/ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የፓርቲው ጉባኤ ውህደቱን የተቀበለ ስለመሆኑ የሚገልፅ ውሳኔ፣

ለ/ ፓርቲዎቹ ስለውህደቱ ዝርዝር ጉዳዮች ያደረጉት የጽሁፍ ስምምነት፣ እና

ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ሲዋሀዱ የሚኖረው አዲስ ስምና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 67 የተዘረዘሩት ሰነዶች፡፡

4/ ቦርዱ የቀረበለት የውህደት ጥያቄ በዚህ ህግ መሰረት ቀርቧል ብሎ ሲያምን ፤

ሀ/ ለተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሰጥቶ የነበረውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰርዛል፣ አዲሱን ፓርቲ በዚህ ህግ መሠረት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይመዘግባል፤

ለ/ ቦርዱ የእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ንብረት፣ ገንዘብና አስፈላጊ ሰነዶች በውህደት ወደ ተመሰረተው የፖለቲካ ፓርቲ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲተላለፍ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

5/ በውህደት የሚመሠረት የፖለቲካ ፓርቲ እንደ ሁኔታው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 64 ወይም አንቀጽ 65 መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

6/ ውህደት ለመፈጸም የሚፈልገው የፖለቲካ ፓርቲ ለመሰረዝ ወይም ለመፍረስ በሚያደርስ የወንጀል ክስ የቀረበበት እንደሆነ ፓርቲው ክሱ ውሳኔ ሳያገኝ ወይም ሳይዘጋ ሊዋሀድ አይችልም፡፡

## 92. የፖለቲካ ፓርቲ መዋሀድ የሚያስከትለው ውጤት

1/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 91/4/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውህደት ውጤት የሆነው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ/ የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ወራሽ ይሆናል፣

ለ/ የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች መብትና ግዴታ ይተላለፍለታል፣

ሐ/ የተዋሃዱትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለፈ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በቦርዱ ሲጠየቅ ያቀርባል፣

መ/ የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ በፊት ያለባቸውን ፍርድ ወይም መብት ወይም በአንቀጽ 91 ንዑስ አንቀጽ (6) የተመለከተውን የወንጀል ክስ ሳይጨምር፣ የፍትሐብሔር ወይም አስተዳደራዊ ክርክር ተተክቶ ያስፈጽማል፣ ይፈጽማል፡፡

2/ የውህደቱ ውጤት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ በተመዘገበ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ውህደቱ ያስገኘውን ሀብት፣ ንብረትና ዕዳ የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 112 እና 114 መሠረት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

3/ ውህደት የፈጠሩ ፖለቲካ ፓርቲዎች አባል የነበረና በማናቸውም ደረጃ ያሉ ም/ቤቶች ተመራጭ ሆኖ በማገልገል ላይ የነበረ ሰው በውህደቱ የተፈጠረው የፖለቲካ ፓርቲ

አባል ሆኖ መቀጠል የማይፈልግ ከሆነ የግል ተመራጭ እንደሆነ ተቆጥሮ የቀረውን የምርጫ ዘመን ያጠናቅቃል፡፡

## 93. ግንባር ስለመፍጠር

1/ የራሳቸው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና አባላት ያላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ግንባር መፍጠር ይችላሉ፡፡

2/ ግንባር ለመፍጠር የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

ሀ/ እያንዳንዱ ፓርቲ የግንባሩን ምስረታ የተቀበለ መሆኑን የሚገልፅ የጉባኤ ውሳኔ፣

ለ/ ፓርቲዎቹ ስለሚመሰርቱት ግንባር ዝርዝር ጉዳዮች ያደረጉት የጽሑፍ ስምምነት፣ እና

ሐ/ ግንባሩ የሚኖረው ስም እና እንደአስፈላጊነቱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 67 የተዘረዘሩ ሰነዶችን፡፡

3/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ግንባር ለመፍጠር የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን ለቦርዱ በጽሑፍ ያቀርባሉ፣ ቦርዱም በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ምዝገባውን ይፈፀማል፡፡

4/ ቦርዱ ከላይ የተመለከቱ ሁኔታዎችን አሟልቶ የቀረበን የግንባር ምሥረታ ጥያቄ ተቀብሎ፤

ሀ/ የግንባሩ አባል ድርጅቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሳይሰረዝ ለግንባሩ ሌላ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይሰጠዋል፡፡

ለ/ የእያንዳንዱ የግንባሩ አባል ድርጅቶች በተናጠል የሚኖራቸው ሀብትና ንብረት እንደተጠበቀ ሆኖ ግንባሩ የራሱ ሀብትና ንብረት ይኖረዋል፡፡

## 94. የፖለቲካ ፓርቲዎች መቀናጀት

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተወሰነ ጊዜ እና በተወሰኑ ጉዳዮች ዙሪያ ተቀናጅተው እንደ ሁኔታው በሃገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ፡፡

2/ ተቀናጅተው ለመንቀሳቀስ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው በየፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው ከፍተኛ አመራር የተስማማበት መሆኑን የሚገልጽ ሰነድ በማያያዝ የፅሁፍ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው፡፡

ቦርዱ የመቀናጀት ጥያቄው በዚህ ህግ የቀረበ መሆኑን አረጋግጦ ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

3/ ለመቀናጀት የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ እንቅስቃሴ የስምምነት ነጥቦችን የያዘ ሰነድ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ የተደነገገው ቢኖርም እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ሕጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቀጥላል፡፡

## 95. የፖለቲካ ፓርቲ መተካት

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው ጉባዔ ውሳኔ ስሙንና ፕሮግራሙን ለውጦ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

2/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት በአዲስነት የተቋቋመው የፖለቲካ ፓርቲ የፈረሰው የፖለቲካ ፓርቲ ሀብት እና ንብረት ይተላለፍለታል፡፡

3/ አዲስ የተተካው የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት መመዝገብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሰባት
## የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ

## 96. የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ መሰረዝ

የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ምክንያት ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰረዝ ይችላል፤

1/ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በራሱ ፈቃድ ከምዝገባ እንዲሰረዝ ሲጠይቅ፣

2/ በህግ መሠረት ቦርዱ ሲወስን ወይም

3/ የፖለቲካ ፓርቲው ከምዝገባ እንዲሰረዝ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት-ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጥ፡፡

## 97. በፖለቲካ ፓርቲው ጥያቄ ከምዝገባ ስለመሰረዝ

1/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ራሱ ከፖለቲካ ፓርቲነት እንዲሰረዝ ቦርዱን በጽሑፍ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

2/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ከፖለቲካ ፓርቲነት ለመሰረዝ የቀረበ ማመልከቻ በፓርቲው መሪ የተፈረመ መሆን ይገባዋል፡፡

3/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ ከተገለፀው ማመልከቻ ጋር የሚከተለውን አያይዞ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፤

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲውን የኦዲት፣ የሃብትና ንብረት መግለጫ ሪፖርት፣ እና

ለ/ ስለፓርቲው መፍረስ በፖለቲካ ፓርቲው ጉባዔ የተወሰነበት ሰነድ፡፡

4/ ከፖለቲካ ፓርቲነት ለመሰረዝ ማመልከቻ ባቀረበ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ላይ ተቃውሞ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞ ማቅረብ እንዲችል ቦርድ የመሠረዝ ማመልከቻ መቅረቡን በተለያየ የማስታወቂያ መንገድ ለሕዝብ ይገልፃል፡፡

5/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /4/ መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ15 ቀናት ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡ ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲውን አይሰርዝም፡፡

6/ በዚህ አንቀፅ መሠረት ቦርዱ ለመሰረዝ ላመለከተው ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተው ጊዜ ባበቃ በ30 ቀናት ውስጥ ለጠያቂው ፓርቲ በጥያቄው መሠረት ከፓለቲካ ፓርቲነት መሰረዙን በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡ የፓርቲውን መፍረስም ሕዝቡ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

## 98. የፖለቲካ ፓርቲን በቦርዱ ውሳኔ ከምዝገባ ስለመሰረዝ

1/ ቦርዱ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ ሊሰርዝ ይችላል፤

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲው የስም፣ የመለያ ምልክት፣ የሰነድ፣ የአመራር፣ የዋና ጽሕፈት ቤት እና የመሳሰለውን ለውጥ ሲያደርግ ያለ በቂ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነና ይህንኑ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲያስተካክል በቦርዱ ተጠይቆ ሳያስተካከል የቀረ እንደሆነ፣

ለ/ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ ማቅረብ ያለበትን ዓመታዊ የስራ፣ የሂሳብ፣ ወይም ሌሎች ሪፖርቶች በአዋጁ በተወሰነው ጊዜ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነና ይህንኑ በ30 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ በቦርዱ ተጠይቆ ያለ በቂ ምክንያት ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፣

ሐ/ የፓለቲካ ፓርቲው በዚህ አዋጅ እና በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የአባላት ጠቅላላ ጉባኤ ማካሄድ ከሚገባው ጊዜ በሦስት ወር የዘገየ እንደሆነ እና ከዚህ በኋላ ቦርዱ በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጉባኤውን ሳያካሂድ የቀረ እንደሆነ፣

መ/ የፖለቲካ ፓርቲው በሁለት ተከታታይ የምርጫ ወቅቶች በጠቅላላ ወይም የአካባቢ ምርጫ ውድድር ሳይሳተፍ የቀረ እንደሆነ፣

ሠ/ የፖለቲካ ፓርቲው በማጭበርበር ወይም እያወቀ ወይም ማወቅ የተገባው ሆኖ ሳለ አሳሳች መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ከሆነ ወይም በዚህ ሕግ መሠረት መረጃ ሲጠየቅ የሃሰት መረጃ ለቦርዱ የሰጠ እንደሆነ፡፡

ረ/ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፓለቲካ ፓርቲው ኃይልን መሠረት ያደረገ የአመጻ ተግባር፣ ከሙስና ጋር ተያያዥነት ያላቸው የወንጀል ድርጊቶች እና የማጭበርበር ድርጊቶች የፈጸመ እንደሆነ ፤

2/ ቦርዱ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንኡስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት ምክንያቶች ጋር ተመጣጣኝ የሆኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችን ጥሷል ብሎ ሲያምን ፓርቲው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ስህተቱን እንዲያስተካክል የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡፡ በማስጠንቀቂያው መሠረት ያላስተካከለ እንደሆነ እንደ አግባብነቱ ከምዝገባ ሊሰርዘው ይችላል፡፡

3/ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት በተጠሪው የፖለቲካ ፓርቲ ላይ ውሳኔ ከማሳለፉ በፊት ፓርቲው መከላከያውን አቅርቦ እንዲያሰማ ማድረግ አለበት፡፡ ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲውን ከምዝገባ ከመሰረዙ በፊት ፓርቲው ታግዶ እንዲቆይ ሊወስን ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ መሠረት ቦርዱ ያሳለፈውን ውሳኔ የተቃወመ የፖለቲካ ፓርቲ ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

### 99. የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ ውጤት

1/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ፣በቦርዱ ወይም በፍ/ቤት ውሳኔ ሲፈርስ የፓርቲው ንብረት ላለበት ዕዳ መሸፈኛ ይውላል፡፡

2/ የፖለቲካ ፓርቲው ዕዳ የሌለበት ከሆነ ወይም ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ዕዳውን ከፍሎ የተረፈ ቢኖር ቀሪው ገንዘብና ንብረት በቦርዱ ትእዛዝ ለሥነ ዜጋና መራጮች ትምህርት እንዲውል ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## ስለፖለቲካ ፓርቲዎች የገቢ ምንጭ እና የንብረት ሁኔታ
## ንዑስ ክፍል አንድ
## ከመንግስት ስለሚሰጥ ድጋፍ

### 100. በመንግስት የሚሰጥ ድጋፍ መጠንና መስፈርቶቹ

1/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሕጋዊ ሥራቸውን ለማከናወንና ኃላፊነቶቻቸውን ለመወጣት ይችሉ ዘንድ መንግሥት እያንዳንዱ ፓርቲ በፌዴራል እና በክልል ምክር ቤቶች

ምርጫዎች በሚያገኘው የመራጮች ድምጽ፣ ከአባላቱና ደጋፊዎቹ በሚያገኘው መዋጮ፥ ክፍያና ስጦታ፣ በእጩነት በሚያቀርባቸው ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ቁጥር እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መስፈርቶች ላይ የተመሰረተ ዓመታዊ የገንዘብ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

2/ ከላይ በንኡስ አንቀጽ (1) በተመለከተው መሠረት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ መጠን በሚከተሉት መስፈርቶች መሠረት ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤

ሀ/ ለፌዴራል እና ለክልል ምክር ቤቶች በተደረጉ ምርጫዎች ያገኘው የመራጮች ድምጽ ብዛት

ለ/ ከአባላቱና ደጋፊዎቹ ከሚያገኘው ገቢ መጠን

ሐ/ ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የሴት እጩዎች ብዛት

መ/ የፓርቲው የሴቶች አባላት ብዛት እና የ ሴቶች አመራር አባላት ብዛት

ሠ/ ፓርቲው ለውድድር የሚያቀርባቸው የአካል ጉዳተኛ እጩዎች ብዛት

3/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 2(ሀ) የተደነገገው ቢኖርም አንድ ፓርቲ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተሰጠው ጠቅላላ የመራጮች ድምጽ ያገኘው ዜሮ ነጥብ አምስት ከመቶ (0.5%) ወይም ለተወዳደረበት የክልል ምክር ቤት አንድ ከመቶ (1%) ያነሰ ከሆነ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ አያገኝም፡፡ ሆኖም ይህ የመቶኛ ቅድመ ሁኔታ አነስተኛ ቁጥር ያለውን ብሔረሰብ ወይም ህዝብ ለመወከል የተደራጁ ፓርቲዎችን አይመለከትም፡፡

4/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሠረት መንግሥት የሚያደርገው የገንዘብ ድጋፍ የዚህን አዋጅ መጽደቅ ተከትሎ በሚካሄደው ጠቅላላ ምርጫ እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

5/ መንግሥት ከላይ ከተገጸው የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ የቁሳቁስና የአገልግሎት ድጋፎችን ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 101. በመንግሥት ስለሚሰጥ ድጋፍ ምንጭ

በመንግሥት የሚሰጠው ድጋፍ፤

1/ ከመንግሥት የሚመደብ፣

2/ ከውጪም ሆነ ከሀገር ውስጥ ከሚገኝ ድጋፍ ወይም እርዳታ እና

3/ ከሌላ ከማንኛውም አካል የሚመነጭ ነው፡፡

## 102. መ ር ሀ

1/ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የመንግሥት ድጋፍ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት በፍትሃዊነት እና ያለ አድልዎ መፈጸም አለበት፡፡

2/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ተግባር ማዋላቸውን የሚያሳውቁበት የግልጽነትና የተጠየቂነት መርህ መከተል አለባቸው፡፡

## 103. በመንግሥት የሚሰጥ ድጋፍ አስተዳደርና የሚከፋፈልበት ሁኔታ

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 100 (2) መሠረት በመንግስት የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ የሚተዳደረውና የሚከፋፈለው በቦርዱ ነው፡፡ ቦርዱ ለዚህ ተግባር አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ይይዛል፡፡

2/ በመንግስት የሚሰጠው ዓመታዊ የገንዘብ ድጋፍ በሁለት ጊዜ ክፍያ የሚፈፀም ይሆናል፤

3/ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 100(2) መሠረት በበጀት አመቱ የሚሰጣቸው የገንዘብ ድጋፍ መጠን ተሰልቶ እንዲሰጣቸው ከመስከረም 30 ቀን በፊት ጥያቄ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረገውን ድጋፍ መጠን እስከ ነሃሴ 30 ቀን ድረስ መወሰን አለበት፡፡

4/ ቦርዱ ከላይ በንኡስ አንቀጽ (3) መሠረት ጥያቄ ሲቀርብለት የፖለቲካ ፓርቲው በሚያቀርበው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የሚገባውን የገንዘብ መጠን ይሰጣል፡፡ ሆኖም በበጀት አመቱ የገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጠው ለሚጠይቅ የፖለቲካ ፓርቲ ገንዘቡን ከመስጠቱ በፊት ቦርዱ ፓርቲው በተጠናቀቀው የበጀት አመት በመንግስት የተሰጠን የገንዘብ ድጋፍ የሂሳብ መዝገብ አስቀርቦ መመርመርና ችግር እንደሌለበት ማረጋገጥ አለበት፡፡ ቦርዱ ፓርቲው የሂሳብ መዝገብ ምርመራ ሪፖርት የሚያቀርብበትን ጊዜ በአንድ ወር ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

5/ በዚህ አዋጅ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲ የሚሰጥ ድጋፍ፤

ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲው የመንግሥት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ከየሚያደርጉት መስፈርቶች ውስጥ ያጓደለው ነገር ሲኖር ይቋረጣል፣

ለ/ መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ መጠቀም አይችልም፣

ሐ/ መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

መ/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4(ለ) እና (ሐ) የተደነገጉት ቢኖሩም የፖለቲካ ፓርቲው የተሰጠውን ድጋፍ ሥራ ላይ ለማዋል መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን አስቀድሞ የገባቸው የውል ግዴታዎች ካሉ ቦርዱ ተመላሽ መደረግ ከሚገባው ገንዘብ ታሳቢ ሊያደርግለት ይችላል፡፡

## 104. ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ ድጋፍ ስለሚመራበት አሰራር

1/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፍ አጠቃቀማቸውን በወጪ አርዕስት በመዘርዘር በኦዲተር ወይም በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡

2/ ቦርዱ መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠውን ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ መመርያ ያወጣል፡፡

## 105. የፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ አያያዝ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ/ በመንግስት የሚሰጠውን ድጋፍ በአገር ውስጥ ባለ ባንክ በተከፈተ የተለየ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት፣

ለ/ ከተፈቀደለት መጠን በላይ ወጪ ሳያደርግ ሂሳቡን በህግ መሠረት ማንቀሳቀስ አለበት ፣

ሐ/ የተሰጠውን ድጋፍ በተለየ የሂሳብ መዝገብ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መያዝ አለበት፣

መ/ በፋይናንስ ህግ መሠረት በበጀት ዓመቱ ከመንግሥት የተሰጠውን የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡን ለምን ተግባር እንዳዋለ የሚያሳይ በኦዲተር ወይም በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ኦዲተሩ ወይም የሂሳብ ባለሙያው የመረመረውን ሂሳብ ከህግና መመርያ ውጭ ወጪ የተደረገ መሆን አለመሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ ላይ አስተያየት መስጠት አለበት፡፡

3/ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከመንግሥት የተሰጠን ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ በማንኛውም ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መመርመር ይችላል፡፡

## 106. ስለተጠያቂነት እና ቅጣት

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ ከታለመለት ዓላማ ውጪ ካዋለ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ ወይም ሐሰተኛ የሂሳብ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣ ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር በተያያዘ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሀ/ የሚሰጠው ድጋፍ ሊቀነስበት ወይም ሊቋረጥበት ይችላል፣

ለ/ ፓርቲው በዚህ አዋጅና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ተገቢው ቅጣት ሊወሰንበት ይችላል፡፡

ሐ/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1)(ለ) ስር የተመለከተው ቅጣት በፓርቲው ኃላፊ ወይም ኃላፊዎችም ላይ ሊፈጸም ይችላል፡፡

3/ ቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲ አላግባብ ወጪ የሆነን ገንዘብ ክስ በመመስረት ወይም በማቻቻል ሊያስመልስ ይችላል፡፡

## 107. ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሚቀርብ የሂሳብ ሪፖርት

1/ ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተደረገውን ድጋፍ አስመልክቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ ሪፖርት፤

ሀ/ በበጀት ዓመቱ ለፓርቲዎች ድጋፍ እንዲውል በመንግሥት የተመደበውንና ከሌላ ምንጭ የተገኘውን ጠቅላላ መጠን፣

ለ/ በበጀት ዓመቱ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የተመደበውን የድጋፍ መጠን፣

ሐ/ ህግ በሚፈቅደው መሠረት በእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በበጀት ዓመቱ ወጪ የተደረገ የገንዘብ መጠን፣

መ/ በበጀት ዓመቱ የታየውን የሂሳብ ሚዛን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

2/ ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ሪፖርት ለዋናው ኦዲተር ጭምር መላክ አለበት፡፡

3/ ዋና ኦዲተሩ ይህ የሂሳብ ሪፖርት በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ በጉዳዩ የሚያዘጋጀውን የሂሳብ መግለጫ ጋር በማያያዝ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ አለበት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የገቢ ምንጭ

## 108. የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ

1/ የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ፤

ሀ/ ከአባላቱ የሚሰበሰብ የአባልነት መዋጮ፣

ለ/ ቦርዱ አጥንቶ በሚያስቀምጠው ጣሪያ መሠረት በኢትዮጵያዉያን ግለሰቦች ወይም ኢትዮጵያውያን በሚቆጣጠሩዋቸው ኩባንያዎች የሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፣

ሐ/ ከአንቀጽ 100 በተደነገገው መሠረት ከመንግሥት ከሚሰጠው ድጋፍና ዕርዳታ፣ ሊሆን ይችላል፡፡

2/ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ አቅሙን ለማጎልበት የሚያግዙ የገቢ ማስገኛዝግጅቶች በማደራጀት ገንዘብ ለማሰባሰብ ይችላል፡፡

3/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ 66 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በንግድና ኢንዱስትሪ ሥራዎች መሰማራት አይችልም፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 109. ከመቀበል የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሰዎች ወይም አካላት የሚቀርብለትን ስጦታ ወይም እርዳታ መቀበል አይችልም፤

ሀ/ ከውጪ ሀገር ዜጎች ተቋማት ወይም ድርጅቶች

ለ/ ከውጪ ሀገር መንግሥት ወይም ከውጪ ሀገር የፖለቲካ ድርጅት፣

ሐ/ ከበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣

መ/ ከሃይማኖት ድርጅት፣

ሠ/ ከፍርድ እስረኞች፣

ረ/ በህገ-መንግስቱ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሥልጣን ለመያዝ ከተደራጀ ቡድን ወይም ሰው፣

ሰ/ በሽብርተኛነት ከተመደበ ድርጅት፣

ሸ/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 111 (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ካልታወቀ ምንጭ የሚቀርብ ስጦታ ወይም እርዳታ፣

ቀ/ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመንግስት ከሆኑ የልማት ድርጅቶ፣

በ/ አንድን ነገር ወደፊት ለማስፈጸም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ከህግ ውጭ ጥቅም ለማግኘት ከሚያልም ማንኛውም አካል የሚሰጥ ስጦታ ወይም እርዳታ፡፡

2/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ በማንኛውም መንገድ የተቀበለ እንደሆነ ስጦታውን ወይም እርዳታውን በተቀበለ በ21 ቀናት ውስጥ ከተያያዥ መረጃዎች ጋር ለቦርዱ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

## 110. ከህግ ውጭ ስለተገኘ ሀብትና ንብረት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ከተፈቀደለት ውጭ ገንዘብ፣ ወይም ንብረት፣ በስጦታ፣ በዳረጎት፣ በውርስ፣ በንግድና ኢንዳስትሪ ሥራ ወይም በማናቸውም መንገድ ተቀብሎ ቢገኝ ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ሦስት እጥፍ ይቀጣል፤ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት
## ስለማህደር፣ ሂሳብ አያያዝና ቁጥጥር

## 111. የፖለቲካ ፓርቲ ማህደርና ኦዲት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ ትክክለኛና ቋሚ ማህደር በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በአግባቡ መያዝ አለበት፤

1/ ማንኛውም በዓይነትም ሆነ በገንዘብ የሚደረግ መዋጮ፣ ስጦታ፣ እና ቃል የተገባለት ስጦታ ወይም መዋጮ፣

2/ ከዚህ የሚከተሉትን ያካተተ የሂሳብ መግለጫ፤

ሀ/ የተለያዩ የገቢ ምንጮችን በሚያሳይ መልኩ የተደራጀ የፓርቲው የገንዘብ ምንጭ ዝርዝር፣

ለ/ ከ 5000 ብር በላይ መዋጮ ያደረገውን ወይም ስጦታ የሰጠውን ወይም ቃል የገባውን ሰው ስም፣

ሐ/ ቃል የተገባ መዋጮ ወይም ስጦታ ካለና የሚከፈልበት ጊዜ፣ እና

መ/ አጠቃላይ የፖለቲካ ፓርቲው የሂሳብ እንቅስቃሴ፡፡

3/ የፖለቲካ ፓርቲ ቋሚ ንብረቶች ዝርዝር፣ መቼ እና እንዴት በባለቤትነት እንደያዘው፣

4/ የፖለቲካ ፓርቲውን የእዳ ዝርዝር፣

5/ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቦርዱ የሚፈልጋቸው ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች፡፡

## 112. የሂሳብ መዝገብ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጭ ሂሳብ አያያዝ ሥርአት ይኖረዋል፡፡

2/ የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጭ ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት በሂሳብ አያያዝ ልምድ ተቀባይነት ባለው መንገድ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

3/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በማንኛውም ጊዜ አባል የሆነበትን የፓርቲውን የገቢና ወጭ ሂሳብ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

4/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚያወጣቸው ወጪዎች ሁሉ ለፖለቲካ አላማው መዋላቸውን ለቦርዱ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

## 113. ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በየዓመቱ በራሱ ኦዲተር የሂሳብ ምርመራ ያካሂዳል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲው በቦርዱ ከተመዘገበ ከስድስት ወር ጀምሮ የሂሳብ ሪፖርቱን የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በሶስተኛው ወር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለቦርዱ የሚያቀርበው አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት፤

ሀ/ ዝርዝር የገቢ መጠን እና የገቢ ምንጭ፣

ለ/ የወጪ አርእስቶችን የያዘ የወጪ ዝርዝር፣

ሐ/ የቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችና ዕዳ ዝርዝር መግለጫ፣ እና

መ/ ስለትክክለኛነቱ የፖለቲካ ፓርቲው መሪ ፈርሞበት በፓርቲው ማህተም የተረጋገጠ ሰነድን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

3/ ፓርቲው ከላይ የተመለከቱትን የገቢ፣ የወጪ፣ የንብረትና እዳ ዝርዝር መግለጫዎች ለቦርዱ ከነማብራሪያቸው ማቅረብ አለበት፡፡

4/ በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የዓመት የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ በይፋ ያወጣል፡፡ ይህ የዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በዚህ አዋጅ መሠረት ተመርምሮ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይገባዋል፡፡

5/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ሪፖርት ካላቀረበ ወይም ፓርቲው ሪፖርት አቅርቦም ቦርዱ በተላከለት ሪፖርት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው ቦርዱ የውጭ ኦዲተር በመላክ ሂሳቡ እንዲመረመር ያደርጋል፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለምርጫታዛቢዎች፣የዕጩ ወኪሎች፣ጋዜጠኞችና የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ

### 114. ስለ ምርጫ ታዛቢዎች

1 የምርጫ ሂደት ለመታዘብ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ለቦርዱ በማመልከትና ሲፈቀድላቸው የሚሰጣቸውን የታዛቢነት የምስክር ወረቀት በመያዝ ምርጫ ለመታዘብ ይችላሉ፡፡

2 የውጭ የምርጫ ታዛቢዎች አገሪቱ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት በመንግሥት ግብዣ ምርጫ ለመታዘብ ይችላሉ፡፡

3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ምርጫን የሚታዘብ የውጭ ታዛቢ ቡድን ወይም ድርጅት ከቦርዱ የታዛቢነት የምስክር ወረቀት መውሰድ አለበት፡፡

4 ምርጫውን ለመታዘብ የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች በቦርዱ የሚዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የሥነምግባር መመሪያ መቀበላቸውን በድርጅቶቹና በወኪሎቻቸው ፊርማ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

5 ቦርዱ ምርጫ ለመታዘብ ከተፈቀደላቸው ታዛቢዎች ጋር በመመካከር ታዛቢ ቡድኖቹን ያሰማራል ፡፡

### 115. የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች

1. ቦርዱ የምርጫ ታዛቢነት ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት፤

   ሀ. ህጋዊ ሰውነት ያለው አገር በቀል ድርጅት መሆኑን፣

   ለ. ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻና ለትርፍ ያልተቋቋመ መሆኑን፥ እንዲሁም የማንኛውም መንግስታዊ ተቋም አካል አለመሆኑን

   ሐ. የድርጅቱ የቦርድ ኣባላትና መሪዎች የማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ አባላት አለመሆናቸውን፤

መ. ድርጅቱ የሚያሰማራቸው ግለሰቦች ምርጫ በገለልተኝነት ለመታዘብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን በማጣራትና ድርጅቱ ያለውን የማስፈጸም አቅም አረጋግጾ በቦርዱ የተዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የሥነ ምግባር ደንብ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም አረጋግጦ የታዛቢነት ሰርቲፊኬት ይሰጠዋል፡፡

ሠ. በዚህ ንዑስ አንቀጽ ከሀ እስከ መ ድረስ የተዘረዘሩትን በተመለከተ ቦርዱ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል፡ ፡

2. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ(1) የተደነገገው ባለመሟላቱ ምክንያት የቀረበለትን የታዛቢነት ማመልከቻ ያልተቀበለ እንደሆነ ይህን ውሳኔውን ማመልከቻውን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡ አመልካቹ በቦርዱ ውሳኔ ካልተስማማ በ14 ቀን ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ከሥነ ምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደ አግባብነቱ የተፈጸመውን ስህተቱ ጠቅሶ ለግለሰቡና ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲታረም ለማዘዝ አልያም ግለሰቡ ወይም ወካዩ ድርጅት ከታዛቢነት ለማገድ ይችላል፡፡

## 116. የምርጫ ታዛቢዎች መብት

1. የምርጫ ታዛቢነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የድርጅት ወኪል በምርጫ ጣቢያ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት መብት አለው፡፡ታዛቢዎች የምርጫ ሰነዶችን የመመልከት፤ የድምጽ አሰጣጥ እና የድምጽ ቆጠራ ሂደቱን የመታዘብ መብት አላቸው፡፡
2. የምርጫ ታዛቢዎች በምርጫው ሂደት የታዘቧቸውን ወይም ያጋጠሟቸውን ጉድለቶች ለቦርዱ ጽህፈት ቤት የማቅረብ መብት አላቸው፡፡ዝርዝሩ በቦርዱ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 117. የምርጫ ታዛቢዎች ግዴታ

ከቦርዱ የምርጫ ታዛቢነት የምስክር ወረቀት ያገኘ የምርጫ ታዛቢ፡-

1. የታዛቢነት መታወቂያውን መያዝና ሲጠየቅ ማሳየት አለበት፡፡

2. የምርጫ አስፈፃሚዎች የሚሰጡትን መመሪያ ማክበር አለበት፡፡

3. የምርጫው ሂደት በትክክልና በብቃት እንዳይካሄድ ከሚያደናቅፍ ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡

8. ቦርዱ ያወጣውን የስነ-ምግባር ደንብ ማክበር አለበት፡፡

9. ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

6 ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ የምርጫ ታዛቢ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በገለልተኝነት፣ የሀገሪቱን ሕጎች ፣ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን እና የቦርዱን መመሪያ በማክበር የምርጫውን ሂደት መታዘብ ይችላል፡፡

## 118. የፖለቲካ ፓርቲ እና የግል ዕጩ ወኪሎች

1. ማንኛውም ለምርጫ ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ የምርጫውን ሂደት የሚከታተሉ፡-

   ሀ. ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት ሁለት እየተቀያየሩ የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎች፣

   ለ. በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር በሚገኝ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ እየተቀያየሩ በጣቢያው የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎችን መሰየም ይችላል፡፡

2. ማንኛውም የግል ዕጩ፡-

   ሀ. በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽ/ቤት ሁለት እየተቀያየሩ የሚሰሩ ተቀማጭ ወኪሎች፡

   ለ. በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር በሚገኝ በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ በፈረቃ በጣቢያው የሚቀመጡ ሁለት ወኪሎችን መሰየም ይችላል፡፡

3. እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ በአንድ የምርጫ ክልል ከሰባት የማይበልጡ ተዘዋዋሪ ወኪሎችን መመደብ ይችላል፡፡

## 119 የወኪሎችን ስም ዝርዝር ስለማሳወቅ

1. ማንኛውም ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ የተቀማጭና የተዘዋዋሪ ወኪሎችን ስም ዝርዝር ተጠባባቂ ወኪሎችን ጨምሮ ከድምፅ መስጫው ዕለት ሰባት ቀን አስቀድሞ ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ የምርጫ ክልሉ ኃላፊም የታዛቢዎቹ ስም ዝርዝር የያዘ ደብዳቤ ዝርዝሩ በደረሰው በሁለት ቀናት ውስጥ ለፖለቲካ ፓርቲው መስጠት አለበት፡፡

2. የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በየምርጫ ጣቢያው የተመደቡ ተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎችን ለየምርጫ ጣቢያው በወቅቱ ያሳውቃል፡፡

## 120. የወኪሎች መብት

1 የማንኛውም እጩ ተቀማጭ ወኪል በተመደበበት ቦታ የምርጫውን ሂደት የመከታተል፣ ቅሬታውን በየደረጃው የማቅረብ እና መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

2 በምርጫው ሂደት የታዘባቸውን ጉዳዮች መዝግቦ የመያዝ እና ከምርጫ ጣቢያው ሃላፊዎች ማብራሪያ የመጠየቅ መብት አለው፡፡

3. የማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ተዘዋዋሪ ወኪል በተመደበበት ቦታ የምርጫውን ሂደትን በሚመለከት ተገቢ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡
4. የማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል እጩ ወኪል ያለ ምንም ተፅእኖ በህግ የተሰጠውን የውክልና ተግባር ያከናውናል፡፡

5. የእጩ ወኪል የሆነ ሰው የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ የሚሰጠውን ትእዛዝ ማክበር እና የምርጫ ሂደቱን ከሚያውኩ ተግባራት መቆጠብ አለበት፡፡ ስለአፈጻጸሙ ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 121. የወኪሎች ግዴታ

ማንኛውም ተዘዋዋሪም ሆነ ተቀማጭ ወኪል፡-

1 የምርጫ ኃላፊው የሚሰጠውን ትእዛዞች ማክበር አለበት፡፡

2. አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ መታወቂያውን ማሳየት አለበት፡፡

3. የምርጫ ህጉን ማክበር አለበት፡፡

4. የምርጫውን ሂደት የመከታተል ተግባሩን ሲያከናውን መራጮች ማንን መምረጥ እንዳለባቸው አስተያየት ከመስጠት ወይም ተጽእኖ ለማሳደር መሞከር የለበትም፡፡

5. የምርጫ ቁሳቁሶችን መያዝ፥ ማንሳት፤ መነካካት ወይም በቁሳቁሶቹ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ተግባራትን መፈጸም የለበትም፡፡

6. የምርጫ ጣቢያውን ሃላፊ ወይም ሰራተኛ ከማስፈራራት ወይም ስራውን ከሚያደናቅፉ ተግባራት መቆጠብ አለበት፡፡

7. ወደ ድምጽ መስጫ ክፍሎች መግባት የለበትም፡፡

8. ቦርዱ የሚያወጣውን የወኪሎች የሥነ ምግባር ደንብ መፈረም እና ማክበር ይገባዋል፡፡

## 122. የወኪል አለመኖር

1. ማንኛውምእጩ ወይም የእጩ ወኪል በራሱ ምክንያት በተመደበበት ቦታ ባልተገኘበት ወቅት የተከናወኑ የምርጫ ተግባራት ውድቅ እንዲደረጉ ሲል ለመጠየቅ አይችልም፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ወኪሉ ያልተገኘው ሆን ተብሎ በተቀነባበረ መሰናክል ምክንያት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ወኪሉ ሳይኖር የተከናወኑ የምርጫ

ተግባራት ወኪሉ በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት እንደአግባብነቱ በምርጫ ክልሉ ወይም በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡

## 123. መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት

ቦርዱ ለታዛቢዎች፣ ለተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎች፣ ለጋዜጠኞች እና ለምርጫ ታዛቢዎች መታወቂያ ካርድ አዘጋጅቶ መስጠት አለበት፡፡

## 124. የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት

1. ቦርዱ መራጮች በቂ ምርጫ ነክ ግንዛቤ የሚያገኙበትን ስልት በመቀየስና የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፡፡

2. ቦርዱ የሥነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት መስጠት እንዲችሉ ህጋዊ ሰውነት ላላቸው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችና የትምህርት ተቋማት፤ የማስተማር ፈቃድ ይሰጣል፡፡ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

3. በዚህ አዋጅ መሰረት በቦርዱም ሆነ በቦርዱ ፈቃድ በሚሰጣቸው ተቋማትና ድርጅቶች የሚሰጥ ትመህርትና ስልጠና ቦርዱ የሚያዘጋጃቸውን የማስተማሪያ ሰነዶች መሠረት ያደረገ ይሆናል፡፡

## 125. የፈቃድ አሰጣጥ

መራጮችን ለማስተማር የሚፈልግ ድርጅት ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት ቦርዱ፡-

1. አመልካቹ፡-
    - ሀ. በህግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ አገር በቀል የሲቭል ማህበረሰብ ድርጅት ወይም እውቅና ያለው የከፍተኛ ትምርህት ተቋም መሆኑን፣
    - ለ. ለመራጮች ትምህርት ያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን
    - ሐ. ተግባሩን ለመወጣት የሚያስችል ብቃት ያለው መሆኑን፣
    - መ. ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ገለልተኛ መሆኑን፣

    በማጣራትና ቦርዱ ያዘጋጀውን የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ሥነ ምግባር መመሪያ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም የማስተማር ፈቃድና መታወቂያ ይሰጣል፡፡
2. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩትን ለማያሟላ ድርጅት ፈቃድ አይሰጥም፤ አለመፍቀዱንም ከነምክንያቱ በፅሁፍ ለአመልካች ያሳውቃል፡፡ የስነ ዜጋና መራጮች ትምህርት ለማስተማር አመልክቶ በቦርዱ የተከለከለ ማንኛውም ድርጅት ወይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም የማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ድርጅትም ሆነ ተወካይ ከስነ ምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደ አግባብነቱ ለግለሰቡም ሆነ ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲያርም ለማድረግ ወይም ፈቃዱን እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

126. **ስለጋዜጠኞች**

1. የምርጫ ሂደትን መዘገብ የሚፈልግ ጋዜጠኛ ስራውን የሚገልጽ መታወቂያና ከሚሰራበት የብዙኃን መገናኛ ተቋም የተሰጠ ማረጋገጫ በመያዝ የምርጫውን ሂደት መከታተል ይችላል፡፡ ከምርጫ ጣቢያ 200 ሜትር ርቀት ዙሪያ ውስጥ ገብቶ ለመዘገብ የፈለገ ጋዜጠኛ ከምርጫው ቀን አስቀድሞ ከቦርዱ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

2. ማንኛውም ጋዜጠኛ ከላይ በንዑስ አንቀፅ(1) የተጠቀሰውን ሥራውን ሲያከናውን በመራጮች ውሳኔ ላይ እና ምርጫ አስፈጻሚዎች ተግባራት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድር ድርጊት መቆጠብ አለበት፡፡

3. ማንኛውም ጋዜጠኛ ቦርዱ ከዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ጋር በተጣጣመ መንገድ የሚያወጣውን የምርጫ አዘጋገብ የሥነ ምግባር ደንብ ማክበር አለበት፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>የምርጫ ሥነ ምግባር</u>
## <u>ምዕራፍ አንድ</u>
## <u>የምርጫ ሥነ ምግባር ድንጋጌዎች</u>

127. **መርህ**

1/ በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ሥርዓት የሚመረጥ መንግስት ህጋዊነት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ይመሠረታል፡-

ሀ/ መራጮች በምርጫ ዘመቻው አማካይነት ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲዎችና ስለ እጩዎች ማንነት የተሟላ መረጃ ሲሰጣቸውና የራሳቸውን በእውቀት ላይ በተመሰረተ እና ከግል ፍላጎት የሚመነጭ ውሳኔ ሲያደርጉ፤ እና

ለ/ መራጮች በነፃነት፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለ ፍርሃት፣ ያለ ተፅእኖ፣ ያለ ጫና፥ እንዲሁም ከጉቦ እና ከተለያዩ መደለያዎች ነፃ በሆነ መልኩ ድምፅ መስጠት ሲችሉ፣ ነው፡፡

2/ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በቅን ልቦና እየተመሩ፡-

ሀ/ የምርጫ ሥነ ምግባርመርሆዎች እንዲከበሩ፣

ለ/ ምርጫ የመላው ህዝብ ነፃ እና ተቀባይነት ያለው ውሳኔ መግለጫ ሆኖ እንዲታወቅ፣

ሐ/ የመራጩ ህዝብ ውሳኔ በሁሉም ዘንድ የተከበረ እንዲሆን፣ መስራት አለባቸው፡፡

3/ ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ ማናቸውም ጉዳዮች ዙርያ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎችና የግል እጩ ተወደዳሪዎች ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ አኳኋን መንቀሳቀስ አለባቸው፡፡

## 128. ለአዋጁ የሥነ ምግባር ድንጋጌዎች መገዛት

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ተወዳዳሪ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት መንቀሳቀስ አለበት፤

ለ/ መሪዎቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ እና አባላቱ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንዳይጥሱ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለበት፤

ሐ/ የፓርቲው ኃላፊዎች እጩዎችና አባላት የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የሚጥስ ተግባር እንዳይፈጽሙ፤ ደጋፊዎቹም የተከለከሉ ድርጊቶች ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ለማድረግ የሚያስችሉ ተገቢ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፤

መ/ ዓላማ እና ፕሮግራማቸውን ወደ ሕዝብ በሚያደርሱበት ጊዜ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ያለ አድልዎ ተፈጻሚ ማድረግ አለባቸው፡፡

2/ የፓርቲው አባላት ወይም ደጋፊዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲያከብሩ ቦርዱ በሚያወጣው ዕቅድ መሠረት ማስተማርና ሌሎች ተገቢነት ያላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡፡

3/ ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሥነ-ምግባር የሚያስተምሩበትና አቋማቸውን የሚገልጹበትን መንገድ እንዲሁም የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማቸውን አስመልክቶ ዝርዝር መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

## 129. የምርጫ ዘመቻ አካሄድ

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ/ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ የማካሄድ የፖለቲካ ሀሳቦችንና መርሆዎቻቸውን ያለ ስጋት የማሰራጨት መብቶቻቸውን ማክበር፤

ለ/ እንቅስቃሴው የሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ፣ የመራጩን ሕዝብ እና የሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ያከበረ መሆን፤

ሐ/ የብዙኃን መገናኛ ነፃነትንማክበር፤

መ/ ተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ ያላቸውን የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ ማክበር፤

ሠ/ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ የሚሹ የመምረጥና የመመረጥ መብት ያላቸው ዜጎች ሁሉ  በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ የበኩሉን አስተዋጽዖ ማድረግ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ/ የግል ወይም የመንግስት ጋዜጠኞች በሙያዊ ስራቸው ላይ እንዳይሰማሩ ማዋከብ፣ እንቅፋት መፍጠር፤ በማንኛውም አይነት ድርጊት የሌሎች ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጐል፣ እንዲቋረጥ፣ እንዲበላሽ፣ እንዲዳከም ማድረግና መተባበር፤

ለ/ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ፅሁፍ ወይም ፖስተር  እንዳይሰራጭ ማወክ፤

ሐ/ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ፖስተሮችን ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ እንዳይታዩ ወይም እንዳይነበቡ ማድረግ፤

መ/ ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ  ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ፥ የእግር ጉዞ፥ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርግ በአመራሩ፣ አባላቱ፣ ወይም ደጋፊዎቹ አማካይነት ማገድ፣ ማወክ፣ ቅስቀሳ ማድረግ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ማደናቀፍ፤

ሠ/ ማንኛውም ሰው በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ድጋፍ ሰልፍ እንዳይሳተፍ መከልከል፤

ረ/ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከሉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲፈፅሙ መቀስቀስና ማነሳሳት፤ የለበትም፡፡

## 130. ስለ ምርጫ ሂደት

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1/ ከምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር በመተባበር ድምጽ የመስጠት ሂደቱ በሰላማዊ ሁኔታ፣ የመራጮችን የመምረጥ መብት ከሚያደናቅፉ ማንኛውም ሁኔታዎች በፀዳ፣ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲተገበር መስራት አለበት፡፡

2/ ከምርጫው ዕለት በፊት፥ በዕለቱ ለትና ከምርጫው ቀን በኂላ ባሉት ጊዜያት ሁሉ የምርጫ አስፈጻሚዎችን ደኅንነት ለማረጋገጥ የበኩሉን ማድረግ አለበት

3/ የታዛቢነት ፈቃድ ያላቸውን ታዛቢዎች እና ኃላፊዎች ማክበር እና ከነርሱ መተባበር አለበት፤

4/ የድምጽ አሰጣጥ ሚስጥራዊነትን ማክበርና እንዲከበር ማገዝ አለበት፡፡

5/ የድምጽ መስጫ ጣቢያን በኃይል በመቆጣጠር ወይም በሌላ በማንኛውም ህገወጥ መንገድ ድምፅ ለማግኘት መንቀሳቀስ የለበትም፡፡

6/ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ሥራ፣ እንዲሁም የድምጽ አሳጣጥ ወይም የድምፅ ቆጠራ ሂደትን ማወክ ወይም ያለ አግባብ በሥራውም ሆነ በሂደቱ ጣልቃ መግባት የለበትም፡፡

7/ የድምጽ አሰጣጡ ሚስጥራዊ አይደለም የሚል እንደምታ ያለው የሀሰት መረጃ ለመራጮች መስጠት የለበትም፡፡

## 131. የምርጫ ውጤትን ስለመቀበል

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ በሚመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠን የምርጫ ውጤት መቀበል አለበት፡፡

2/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ ቅሬታውን በሕጉ መሠረት ለሚመለከተው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

3/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ የድምጽ አሰጣጡ ከተጠናቀቀ ከ48 ሰዓት በኋላ በምርጫው ሂደትና ውጤት ላይ ያለውን አስተያየትና ቅሬታ የሚመለከት ይፋዊ መግለጫ ለብዙኃን መገናኛ መስጠት ይችላል፡፡

4/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚሰጥ መግለጫ ይዘት ቅሬታ በተነሳባቸው ነጥቦች ብቻ የተወሰነ ሆኖ መግለጫው በሚሰጥበት ወቅት ባለው ሁኔታ ላይ የሚያተኩር መሆን አለበት፤ በተለይም አጠቃላይ ምርጫውን የሚነቅፍ መሆን የለበትም፡፡

5/ በፖለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ተወዳዳሪ የምርጫ ውጤትን አስመልክቶ የሚሰጥ መግለጫ ግጭትን ከሚቀሰቅስና ተወዳዳሪ ፓርቲም ሆነ ግለሰብን ከሚያጣጥል ቋንቋ የጸዳ መሆን አለበት፡፡

## 132. ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል የቋንቋ ይዘት

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ/ የምረጡኝ ዘመቻውን ሲያደራጅና ሲያካሂድ ለአጠቃላይ የምረጡኝ ዘመቻ፣ ለድምፅ አሰጣጥ፣ ለቆጠራ እና ለድህረ ምርጫ ሂደቱ ሰላማዊነትና ስኬት አስተዋፅኦ በሚያደርግ አኳኋን ማድረግ አለበት፡፡

ለ/ ከሚጣልበት ኃላፊነትና ካለው ክብር ጋር በተመጣጠነ ደረጃ መንቀሳቀስ አለበት፡፡

2/ ማንኛውምሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ንግግር የሚያደርግ ሰው፡-

ሀ/ ግጭት ቀስቃሽ የሆነ ወይም የግል ስብዕናን የሚነካ ቋንቋ ማስወገድ አለበት፡፡

ለ/ በማንኛውም መልኩ ለአመጽ የሚጋብዝና በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ ስጋትን የሚጭር የቋንቋ አጠቃቀም ማስወገድ አለበት፡፡

3/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በይፋም ሆነ በስውር አመፅ የሚቀሰቅስ ወይም የሚያበረታታ የቋንቋ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔት ወይም ፖስተር ማሳተም ወይም ማሰራጨት የለበትም፡፡

## 133. ያልተገባ የምልክቶች አጠቃቀም

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1/ የሌሎች ፓርቲዎችን አርማ ወይም የምርጫ ምልክት በማመሳሰል መጠቀም፤

2/ የሌሎች ፓርቲዎች የፖለቲካ ወይም የምርጫ ቁሳቁስ መስረቅ፣ ምልክት ማንሳት፣ ማበላሸት፥ ማጥፋት፤ወይም

3/ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከለ ማንኛውንም ተግባር እንዲፈጽሙ ማነሳሳት፤ የለበትም፡፡

## 134. ማስፈራራትና አመጽ መቀስቀስ [ክልክል ስለመሆኑ]

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ማንኛውንም አይነት ማስፈራራት ወይም ወከባ የተከለከለ መሆኑን ተቀብሎ፡-

ሀ/ የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች መቼም ቢሆን ማንንም ሰው የሚያስፈራሩ፥ የሚያሸማቅቁና የሚያዋክቡ ድርጊቶችን እንዳይፈጽሙ የሚከለክሉ መመሪያዎች ማውጣት፤

ለ/ አመፅንና አመጽ ቀስቃሽ ድርጊቶችን መቃወምና አባላቱንም ማስተማር፤

ሐ/ በኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ፣ አባላቱ ወይም ደጋፊዎቹ የሚፈፀሙ አውዳሚ ወይም ሰላምን የሚያናጉ ድርጊቶችን ወይም ይህን የሚጋብዝ ዛቻን በመቃወም ማስተማር፤

መ/ የሌላውን ግለሰብ ሆነ ፓርቲ መብት፥ ንብረትና ጥቅሞች ማክበር፤ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ለፖለቲካ የድጋፍ ሰልፍ፥ ለስብሰባ፣ የእግር ጉዞ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሲወጡ ማናቸውንም ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች መያዝ ክልክል መሆኑን ማስተማር አለበት፡፡

3/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፦

ሀ/ ጥንካሬውን ወይም የበላይነቱን ለማሳየት ሲል በማንኛውም የሁከት ወይም የአመጽ እንቅስቃሴ መሳተፍ ወይም እንዲደረግ መፍቀድ የለበትም፤

ለ/ በህዝብ ወይም በግለሰብ ንብረት ላይ ውድመት እንዳይደርስ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ መከላከል አለበት፤

ሐ/ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተደነገጉ ማናቸውንም ክልከላዎች እንዲጥሱ ማነሳሳት የለበትም።

## 135. ስልጣንን ያለ አግባብ መጠቀም

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፦

ሀ/ ያለውን የሥልጣን ኃላፊነትና የተለየ ዕድል ወይም ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ለፖለቲካ ፍላጎቱ ለመጠቀም መደለያ ማቅረብን፣ ቅጣትን ወይም ማንኛውንም ህገወጥተግባር መጠቀም፤

ለ/ የፌዴራል መንግስትን፣ የክልል መንግስትን፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤትን ወይም ሌላ የህዝብ ሀብትን በምርጫ ህጉ ከተፈቀደው አኳኋን ውጭ ለምርጫ ቅስቀሳ ዓላማ መጠቀም፣ የለበትም።

2/ በዚህ ክፍልውስጥ "ስልጣን፣ልዩ መብት ወይም ጫና" ማለት የወላጅ፣ የዝምድና፣ የመንግስት፣ የፖሊስ፣ የአካባቢ ታጣቂ ኃይል፣ የወታደራዊ ወይም ልማዳዊ ወይም ባህላዊ ስልጣንን ያካትታል።

## 136. ስለ ሙስና ተግባር

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፦

1/ ኃይል በመጠቀም ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ አይነት መደለያ በመስጠት መራጩ ህዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ድምፁን ከመስጠት እንዲታቀብ ማድረግ፤

2/ ኃይል በመጠቀም ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ አይነት መደለያ በመስጠት ሰዎች እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነታቸው እንዲወጡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነት እንዳይወጡ ማድረግ፤

3/ ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በሚመራው ወይም በሚሰራበት ተቋም አግባብ ያልሆነ ድጋፍ ወይም እርዳታ በመጠቀም እጩ ተወዳዳሪን ማስተዋወቅ ወይም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን የማስተዋወቅ ዕድል ማደናቀፍ፤ የለበትም።

## 137. ቀጣይ ግንኙነት ስለመፍጠር

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ቀጣይ ግንኙነት ፈጥሮ መንቀሳቀስ ይችላል።

2/ የፓለቲካ ፓርቲዎች የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ጠብቀው ሆኖ በምርጫ ዘመቻ ወቅት እና በማናቸውም ጊዜ በጋራ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት የሚያገለግል የጋራ መድረክ ሊመሰርቱ ይችላሉ።

<u>ምዕራፍሁለት</u>

<u>የባለድርሻ አካላት ኃላፊነት</u>

## 138. የፖለቲካ ፓርቲዎችና እጩ ተወዳዳሪዎች ኃላፊነት

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ ይህ የምርጫ አዋጅ በመራጩ ህዝብ ዘንድ እንዲታወቅ የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት፤ በተለይም አዋጁን ለእጩዎቹ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ በማስተማር በሁሉም ዘንድ መታወቁንና መከበሩን ማረጋገጥ አለበት።

2/ እያንዳንዱየፖለቲካ ፓርቲ በምርጫው ሂደት የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ለመራጮች ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍና ማስተዋወቅ አለበት።

3/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ፦

ሀ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ማክበር፤

ለ/ እጩዎቹ ባለስልጣኖቹ፣ ወኪሎቹ፣ አባሎቹና ደጋፊዎቹ ይህን አዋጅ አክብረው እንዲንቀሳቀሱ መምራት እና ማክበራቸውንም የሚያግዙ ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ፤ አለበት።

4/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ ፤ሁሉም ሰው፦

ሀ/ የፖለቲካ እምነቱን እና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፤

ለ/ በሌሎች የፖለቲካ እምነት እና አስተያየት ላይ የመከራከር እና የመተቸት፤

ሐ/ የራሱን የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁሶች የማተምና የማሰራጨት፤

መ/ ፖስተሮችን፣ባነሮችንናቢልቦርዶችን የመስቀል፤

ሠ/ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ማንኛውም አይነት ገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሰው ኃይል የምርጫ ድጋፍ የማሰባሰብ፤

ረ/ አባላትን የመመልመል፤

ሰ/ ህዝባዊ ስብሰባዎችን የማካሄድ፤

ሸ/ በህዝባዊ ስብሰባዎች የመገኘት፤

ቀ/ መብቶች እንዳሉት በይፋ የመግለፅ ግዴታ አለበት፡፡

5/ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች አዋጁንና በአዋጁም ለመገዛት ያላቸውን ቁርጠኝነት ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው፡፡

6/ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች ነፃና ፍትሀዊ ምርጫን የሚጐዳ ወይም የሚያጣጥል ማንኛውንም ተግባር በይፋ ማውገዝ አለባቸው፡፡

## 139. የቦርዱና የሌሎች የምርጫ አስፈፃሚ አካላት ኃላፊነት

1/ ቦርዱ ይህ አዋጅ በምርጫው ሂደት ላይ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ሚና የሚጫወቱ መንግሥታዊና ሌሎች አካላት ዘንድ እንዲታወቅ ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት፡፡

2/ ቦርዱ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ለሚመለከተው ሁሉ የማሰራጨት ኃላፊነት አለበት፡፡

3/ በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በዚህ አዋጅ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ለሚመለከታቸው ሁሉ ትምህርት መስጠት አለባቸው፡፡

## 140. የሌሎች አካላት ሚና

1/ የመገናኛ ብዙሃን የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አስመልክቶ ለህዝብ ትምህርት እንዲሰጡ ቦርዱ ድጋፍ ያደርግላቸዋል፡፡

2/ በቦርዱ በሚወጣው መመርያ መሰረት ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አስመልክቶ ትምህርት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡

## 141. የፖለቲካ ፓርቲዎች ምክር ቤት

1/ በምርጫየሚወዳደሩየፖለቲካፓርቲዎችየዚህን ክፍል ድንጋጌዎችና ሌሎች የጋራ ጉዳዮችን ተግባራዊ ለማድረግና በምርጫው ሂደት በሚነሱ ልዩ ልዩ የአፈፃፀም፣ የዴሞክራሲ፣ የሰብአዊ መብት ጉዳዮችንና የህግ የበላይነትን በኢትዮጵያ ለማጎልበት በሚያግዙ ጉዳዮች ላይ በመመካከር ችግሮችን እያቃለሉ ለመጓዝ ይችሉ ዘንድ የጋራ ምክር ቤት መመስረት ይችላሉ፡፡

2/ የጋራ ምክር ቤቱ አደረጃጀት፣ አሠራርና ሥርዓት አስመልክቶ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በሚወስኑት መሠረት ይፈጸማል፡፡ሆኖም የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የሚመሠርቱት የጋራ መድረክ አደረጃጀትና የአሠራር ሥርዓት ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር የማይቀረን መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የስነ ምግባር ጥሰቶች እና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

### ንዑስ ክፍልአንድ
### የስነ-ምግባር ጥሰቶች

### 142. መደለያ መስጠትና ኃይልን ወይም ሥልጣንን አለ አግባብ መጠቀም

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ንቅናቄ፣እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1/ ማንኛውንም መደለያ ወይም ጉቦ የሰጠ ወይም የተቀበለ፣

2/ በድምጽ አሰጣጡ ወይም በቆጠራው ጣልቃ የገባ ወይም ያወከ፣

3/ ኃይል በመጠቀም፣ መደለያ በመስጠት ወይም በሌላ በማንኛውም አድራጎት መራጩ ሕዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ከመስጠት እንዲታቀብ ያደረገ፣

4/ የድምጽ መስጫ ጣቢያን በሀይል የተቆጣጠረ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ ድምጽ ለማግኘት የሞከረ፣

5/ ሥልጣኑን መከታ በማድረግ መደለያ ወይም ቅጣት ወይም ሌላ የማስፈራሪያ ዘዴ የተጠቀመ፣

6/ ማንኛውንም መደለያ በመስጠት ኃይል በመጠቀም፣ ወይም በማንኛውም አይነት ድርጊት እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነት እንዲወጡ ወይም እንዳይወጡ ያደረገ፣

7/ የመንግስት ሰራተኛ እና ኃላፊ ሆኖ በራሱ የግል ሳይሆን በመንግስት የስራ ሰዓት እና ኃላፊነት ተቋሙን በመጠቀም እጩዎችን ያስተዋወቀ ወይም ሌሎች እጩዎች ራሳቸውን በሕጋዊ መንገድ እንዳያስተዋውቁ ያደናቀፈ፣

8/ የመንግሥት ንብረት ለምርጫ ቅስቀሳ የተጠቀመ፣ እንደሆነ የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

### 143. ፍርሃት በመቀስቀስ ወይም ሁከት መፍጠር ማንኛውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ማስተጓጎል

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1/ በምርጫ ሂደት ጫና ወይም ተጽዕኖ በመፍጠር ጣልቃ የገባ፣

2/ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎችህሳባቸውንበነጻነት እንዳያስራጩ ስጋት እና ፍርሀት የፈጠረ፣

3/ በማንኛውም መንገድ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የመራጩን ሕዝብ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ ወይም ያወከ፣

4/ ሕዝባዊ ቅስቀሳ ወይም ስብሰባ ወይም ውይይት ወይም ትምህርትና ስልጠና እንዳይካሄድ ያደናቀፈ ወይም ሁከት የፈጠረ፣

5/ ሕዝብ ድምጽ ሲሰጥ ያወከ ወይም ድምጽ እንዳይሰጥ ችግር የፈጠረ፣

6/ የሌሎች ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጐል ወይም እንዲቋረጥ ወይም እንዲበላሽ ወይም እንዲዳከም ያደረገ፣

7/ ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ፣ የእግርጉዞ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ያደናቀፈወይም ሌላ ሰው እንዳይሳተፍ የከለከለ፣

8/ መራጮችን የሰደበ ወይም ያንጓጠጠ ወይም የመምረጥ መብታቸውን ያደናቀፈ፣

9/ ለምርጫው ሂደት የምርጫ አስፈፃሚዎችን እና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ፀጥታና ደህንነት ለማረጋገጥ በሚደረግ ጥረት ከጊዜና ቦታ አኳያ እገዛ ማድረግ እየቻለ ያላደረገ ወይም ያወከ፣

10/ በማንኛውም አይነት መንገድ መራጩ ህዝብ እንዳይመዘገብ ወይም እንዳይመርጥ ያደረገ፣

11/ የድምጽ አሰጣጡን ሚስጥራዊነት ያላከበረ ወይም እንዲከበር እገዛ ማድረግ ሲገባው ያላደረገ፣

12/ የሥነ ምግባር አዋጁ ተጥሷል በሚል ሽፋን የሀሰትና የተጋነነ አቤቱታ በማቅረብ ቅሬታ የማሰማት መብቱን ያለአግባብ የተጠቀመ እንደሆነ፤የሥነ-ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ተቆጥሮ ከምርጫ ውድድር እስከ መታገድ ወይም እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ በሚደርስ ገንዘብ ይቀጣል፡፡

## 144. በምርጫ ሂደት ሰላምና ፀጥታ የሚያናጉ መልዕክቶችን ማስተላለፍ

ማንኛውም የፖለቲካፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1/ የምርጫ ዘመቻውን ሰላም የሚያናጋ ወይም ግጭት የሚቆሰቁስ ወይም አመፅ የሚጋብዝ ወይም ስጋት የሚፈጥር ንግግር ያደረገ፣

2/ በይፋም ሆነ በስውር አመፅን የሚቀሰቅስ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔት ወይም ፖስተር ያሰራጨ፣

3/ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊነት አይጠበቅም የሚል የሀሰት መረጃ የሰጠ፣ እንደሆነ የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

## 145. የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ማደናቀፍ

ማንኛውም የፖለቲካፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1/ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳይመለምልና ጽህፈት ቤት እንዳይከፍት በማናቸውም መንገድ ያደናቀፈ፣ ወይም የተከፈቱ ጽህፈት ቤቶች በነፃነት እንዳይሠራባቸው በግልፅም ሆነ በስውር ያወከ ወይም ሁከት እንዲፈጠር ያደረገ ወይም በማንኛውም ዓይነት ድርጊት የማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ፣

2/ ፓርቲዎች ያዘጋጁት የድርጅት ልሳን፣ የምርጫ ማስታወቂያ፣ በራሪ ጽሑፍ፥ ወይም ፖስተር እንዳይሰራጭ፣ እንዳይታይ ወይም እንዲበላሽ ያደረገ ወይም እንዳይለጠፍ ያወከ ወይም የተለጠፈውን የቀደደ፣ ያበላሸ፣ ያነሳ፥ ያጠፋ፣

3/ የሌላን የፖለቲካ ፓርቲ ምልክት ወይም አርማ የቀዳ ወይም አስመስሎ የተጠቀመ፣

4/ የሌላ ፖለቲካ ፓርቲን የምርጫ ቁሳቁስ የሰረቀ ወይም ያበላሸ ወይም ያጠፋ፣ እንደሆነ፤ የሥነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ተቆጥሮ ከምርጫ ውድድር እስከ መታገድ ወይም እስከ ብር አንድ መቶ ሺህ በሚደርስ ገንዘብ ይቀጣል፡፡

## 146. ከጋዜጠኞች ወይም ከታዛቢዎች ጋር አለመተባበር

ማንኛውም የፖለቲካፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1/ የብዙኃን መገናኛን ነፃነትን የተጋፋ፣

2/ በምርጫ ሂደት ጋዜጠኛን ያዋከበ ወይም ሥራውን ያደናቀፈ፣

3/ የተፈቀደላቸውን ታዛቢዎች ያላከበረ ወይም ያልተባበረ፣እንደሆነ የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

### 147. የሥነ ምግባር ድንጋጌዎቹን አለማስተዋወቅና ሕገ ወጥ ድርጊቶችን አለማውገዝ

አንድ የፖለቲካ ፓርቲ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፦

1/ በአባሉ፣ በአቀረበው እጩ ተወዳዳሪ ወይም በመሪው የተፈፀመን የአመፅ ድርጊት ወይም ለአመፅ የሚጋብዝ ተግባር በይፋ ማውገዝ ሲገባው ያላወገዘ

2/ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ፣ አባላቱና ደጋፊው መቼም፥ ማንንም ማስፈራራት እንደሌለባቸው በግልጽ የሚከለክል መመሪያ ያላወጣ፣ እንደሆነ የስነ ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ተቆጥሮ ቦርዱ የሚወስነውን ቅጣት የሚፈጸምበት ሲሆን የፈጸመው ጥፋት በሌሎች ሕጎችም የሚያስቀጡ እንደሆነ ቦርዱ ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል ሊመራው ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## በተለያዩ አካላት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

### 148. በቦርዱ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

በሌሎች ህጐች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ ከላይ በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል አንድ የተዘረዘሩትን የስነ ምግባር ጥሰቶች በሚያረጋግጥበት ጊዜ የሚከተሉትን እርምጃዎች እንደ ሁኔታው ሊወስድ ይችላል፡፡

1/ ጥፋቱን ለፈፀመ ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ይፋ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

2/ ጥፋቱን የፈፀመ እጩ ወይም ፓርቲ ለአጭር ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ በመገናኛ ብዙሃን እንዳይጠቀም ማገድ፤

3/ ጥፋቱን የፈፀመ ፓርቲ በመንግስት ለፓለቲካ ፓርቲዎች ድጎማ ከሚመድበው ገንዘብ የፓርቲ ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ፤

4/ ጥፋተኛውን የፓርቲ ወይም ግል እጩ ተወዳዳሪ እንደጥፋቱ ክብደት ከምርጫ ተወዳዳሪነት መሰረዝ፤

5/ ጥፋተኛው የፖለቲካ ፓርቲው በምርጫ ውድድር እንዳይሳተፍ ማገድ፡፡
ቦርዱ ከላይ የተዘረዘሩትን ቅጣቶች በጥፋተኛው ላይ ቢያስተላልፍ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ ጉዳዩን ወደ ዓቃቤ ሕግ ሊመራው ይቻላል፡፡

### 149. አቤቱታ ስለማቅረብ

ቦርዱ ከላይ የተመለከቱትን የስነምግባር ጥሰቶች ተከትሎ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 150. በፍርድ ቤት ስለሚወሰኑ ቅጣቶች

1/ ፍርድ ቤት ከላይ ጉዳዩ በቀጥታ ቀርቦለትም ሆነ ቦርዱ በዚህ የህግ ክፍል በሰጠው ውሳኔ የቀረበለትን ቅሬታ በሚመለከትበት ጊዜ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 148 የተደነገጉትን ክልከላዎችና ቅጣቶች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቅጣቶች ጋር በተደራቢነት ሊጥል ይችላል፡፡

2/ በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በድምጽ መስጫ እለት በድምፅ መስጫ ጣቢያ አካባቢ ድምፅ ከመስጠት ወይም የተሰጠን ህጋዊ ተግባር ከማከናወን ውጭ ሌላ ማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ መሳተፍ፣ ወይም ባልተገባ ወይም በተከለከለ ጊዜ የምርጫን ውጤት ማተም፣ ማባዛት፣ ወይም ወይም በዚህ አዋጅ በ አንቀጽ 142 ፣143 እና/ወይም ከዚህ በታች የ ተዘረዘሩትን ጥፋቶች መፈጸም በገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

ሀ/ በቦርዱ ወይም በምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኝነት ጣልቃ ለመግባት የሞከረ፣ በተለይም መደለያ ወይም የተስፋ ቃል የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ፤

ለ/ ምርጫን ለማወክ ወይም እንዳይካሄድ ለማድረግ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም ውጤት ላይ ጫና ለመፍጠር በማሰብ ጥላቻን ወይም ፍርሀትን የሚቀሰቅስ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም በምርጫው ውጤት ላይ ጫና የሚፈጥር የሐሰት መረጃ አሳትሞ ያሰራጨ ወይም ለማሰራጨት ሙከራ ያደረገ፤

ሐ/ የምርጫ ሚስጥራዊነትን የጣሰ

መ/ ከድምጽ እና ከምርጫ ቁሳቁስ ጋር የተያያዙ ክልከላዎችን የተላለፈ፤ ወይም

ሠ/ የቦርዱን ወይም የምርጫ አስፈፃሚዎችን እንቅስቃሴ ያወከ፡

3/ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ወይም የምርጫ ውጤት አገላለፅ፣ የመራጮች ወይም የፓርቲዎችን መብት አስመልክቶ የተጣሉ ክልከላዎችን የጣሰ በገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

4/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ሆን ብሎ የቦርዱ፣ የምርጫ ዋና አስፈፃሚው፣ የቦርዱ ሰራተኛ ስልጣኑን ወይም ተግባሩንና ኃላፊነቱን በሚያከናውንበት ወቅት እንቅፋት የሆነ ወይም ያደናቀፈ እንደሆነ፤ወይም

ለ/ የቦርዱን የስብሰባ ሂደት ሆን ብሎ ያቋረጠ ወይም በነዚሁ ቦታዎች በማንኛውም ሁኔታ ያልተገባ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤ወይም

ሐ/ ሆን ብሎ በቦርዱ የስራ ቦታ ወይም በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ተገቢ ያለሆነ ተጽእኖ ለማሳደር ሲባል ማንኛውም የሀይል ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤ በገንዘብ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

## ክፍል ሰባት
## በምርጫ ሂደት ስለሚነሱ አቤቱታዎችና ክርክሮች

### 151. መርህ

1/ ፍርድ ቤት ከላይ ጉዳዩ በቀጥታ ቀርቦለትም ሆነ ቦርዱ በዚህ የህግ ክፍል በሰጠው ውሳኔ የቀረበለትን ቅሬታ በሚመለከትበት ጊዜ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 148 የተደነገጉትን ክልከላዎችና ቅጣቶች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ቅጣቶች ጋር በተደራቢነት ሊጥል ይችላል፡፡

2/ በሌሎች ህጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በድምጽ መስጫ እለት በድምፅ መስጫ ጣቢያ አካባቢ ድምፅ ከመስጠት ወይም የተሰጠን ህጋዊ ተግባር ከማከናወን ውጭ ሌላ ማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ መሳተፍ፣ ወይም ባልተገባ ወይም በተከለከለ ጊዜ የምርጫን ውጤት ማተም፣ ማባዛት፣ ወይም ወይም በዚህ አዋጅ በ አንቀጽ 142 ፣143 እና/ወይም ከዚህ በታች የ ተዘረዘሩትን ጥፋቶች መፈጸም በገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል፡፡

ሀ/ በቦርዱ ወይም በምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኝነት ጣልቃ ለመግባት የሞከረ፣ በተለይም መደለያ ወይም የተስፋ ቃል የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ፤

ለ/ ምርጫን ለማወክ ወይም እንዳይካሄድ ለማድረግ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም ውጤት ላይ ጫና ለመፍጠር በማሰብ ጥላቻን ወይም ፍርሀትን የሚቀሰቅስ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም በምርጫው ውጤት ላይ ጫና የሚፈጥር የሐሰት መረጃ አሳትሞ ያሰራጨ ወይም ለማሰራጨት ሙከራ ያደረገ፤

ሐ/ የምርጫ ሚስጥራዊነትን የጣሰ

መ/ ከድምጽ እና ከምርጫ ቁሳቁስ ጋር የተያያዙ ክልከላዎችን የተላለፈ፤ ወይም

ሠ/የቦርዱን ወይም የምርጫ አስፈፃሚዎችን እንቅስቃሴ ያወከ፡

3/ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ወይም የምርጫ ውጤት አገላለፅ፣ የመራጮች ወይም የፓርቲዎችን መብት አስመልክቶ የተጣሉ ክልከላዎችን የጣሰ በገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

4/ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ሆን ብሎ የቦርዱ፣ የምርጫ ዋና አስፈፃሚው፣ የቦርዱ ሰራተኛ ስልጣኑን ወይም ተግባሩንና ኃላፊነቱን በሚያከናውንበት ወቅት እንቅፋት የሆነ ወይም ያደናቀፈ እንደሆነ፤ወይም

ለ/ የቦርዱን የስብሰባ ሂደት ሆን ብሎ ያቋረጠ ወይም በነዚሁ ቦታዎች በማንኛውም ሁኔታ ያልተገባ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤ወይም

ሐ / ሆን ብሎ በቦርዱ የስራ ቦታ ወይም በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ተገቢ ያለሆነ ተጽእኖ ለማሳደር ሲባል ማንኛውም የሀይል ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤በገንዘብ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል፡፡

## 152. በመራጮች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

1. ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

2. መብት የሌለው ወይም በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ይሆናል፡፡
4. የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

5. ከላይ በንዑስ አንቀፅ (1) ወይም (2) ለቀረበው አቤቱታ የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ አቤቱታ አቅራቢው ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ 5 ቀናት ውስጥ አቤቱታ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

6. በምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ አቤቱታ ውሳኔ ከተሰጠበት በ5 ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

7. የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

8. ምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ቅሬታ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔያልተስማማ እንደሆነ በ5 ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው የመጀመርያ

ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩ እንዲታይለት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ አቤቱታ የቀረበለት የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

9. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የምርጫ ጣቢያው ፅህፈት ቤት ስራውን ያከናውናል፡፡

## 153. በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

1. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ እንደሆነ ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. አንድ በዕጩነት የተመዘገበ ሰው በእጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሰረት የሚቀርብ አቤቱታ የማቅረቢያ ጊዜ ከእጩዎች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ እጩዎች ይፋ እስከሚሆንበት ቀን ድረስ ይሆናል፡፡

4. የምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮበ 5 ቀናት ውስጥ ውሳኔን በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

5. ለእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ወይም የግል እጩ እንዲሁም የአንድን እጩ ምዝገባ የሚቃወም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት የምርጫ ክልሉን ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በመቃወም በክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለሚቋቋም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ7 ቀናት ውስጥ ቅሬታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

6. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በጽህፈት ቤቱ ሀላፊ ሰብሳቢነት የሚመራ ሆኖ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የሚሰየሙ ሁለት ተጨማሪ አባላት ይኖሩታል፡፡
7. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ሲቀርብለት በ7 ቀናት ውስጥ ውሳኔ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

8. የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በ7 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ችሎቱም የቀረበለትን አቤቱታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር በ15 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል ፡፡

9. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የምርጫ ክልሉ ስራውን ያከናውናል፡፡

## 154. በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

1. አንድ የተመዘገበ መራጭ ድምፅ ከመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ሲፈጠር ቅሬታውን ወዲያውኑ ምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

2. የምርጫጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴም፡-

   ሀ. ጉዳዩን በማጣራት መራጩ ድምጹን እንዲሰጥ ሊወስን ይችላል፣ወይም

   ለ. ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን ወደ ምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል ፣

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሰረትጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ከምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደሁኔታው ስልጣን ካለው የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሳኔ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል፡፡

4. በንዑስ አንቀፅ 2(ሐ) የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የድምፅ መስጫ ሰአት ከማለቁ በፊት ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ የምርጫ ጣቢያውም በውሳኔው መሰረት ይፈፅማል፡፡

5. በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2(ለ) በተመለከተው መሰረት ጊዜያዊ ድምጽ የሰጠ መራጭ ወዲያውኑ ቅሬታውን ስልጣን ላለው የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ችሎቱም የድምጽ ማዳመሩ ሂደት ውሳኔውን እስኪሰጥ ድረስ እንዲዘገይ ሊያዝ ይችላል፡፡

6 የአንድን መራጭ ድምፅ መስጠት የሚቃወም ሰው ከላይ በተደነገገው መሰረት አቤቱታውን በየደረጃው የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

## 155. በድምጽ ቆጠራና ውጤት ስለሚነሱ ክርክሮች

1. በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58(5) መሰረት ወዲያውኑ በማቅረብ ሊያስወስን ይችላል፡፡በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን አቤቱታውን በ2 ቀናት ውስጥ ለምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ2 ቀናት ውስጥ ውሳኔ በጽሁፍ ይሰጣል፡፡

3. በንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በ5 ቀን ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡ቦርዱ የቀረበውን ቅሬታ መርምሮ በ10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

4. በንኡስ አንቀጽ (3) በተሰጠው በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው 10 ቀናት ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱም የቀረበለትን ቅሬታ ለመወሰን የሚያስፈልጉ ማስረጃዎችን አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ለቀረበለት አቤቱታ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ወስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6. ከላይ በተጠቀሱት ንኡሳን አንቀጾች መሰረት በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤቱ ላይ የቀረበ ቅሬታ ወይም ይግባኝ በሚታይበት ጊዜ እንደአግባብነቱ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ቦርዱ ወይም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበበት የምርጫ ክልል ውጤት እንዳይገለጽ ሊያዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት
## የተከለከሉ ተግባራት

### 156. ጠቅላላ

በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ በህዝባዊ ምርጫ እና በድምጽ አሰጣጥ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀልሎችን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ክፍል የተከለከሉ ተግባራትን መፈፀም በሕግ ያስቀጣል፡፡

### 157. የምርጫ ሰነዶችን በህገ ወጥ መንገድ ማተምና መያዝ

ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከቦርዱ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም የምርጫ ሰነድና ቁሳቁስ ያተመ፣ ያባዛ፣ የፈበረከ ወይም በዚህ መልኩ የተዘጋጀን ህገወጥ የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ይዞ የተገኘ ወይም ያደለ እንደሆነ በእስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

### 158. የምርጫ ማስታወቂያን ስለማጥፋት

ማንኛውም ሰው ምርጫ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ውጤት እስከሚገለፅበት ቀን ድረስ የማንኛውንም እጩ ተወዳዳሪ ፖስተርን ወይም የምርጫ ማስታወቂያን ያበላሸ፥ ያስወገደ ወይም የቀደደ እንደሆነ ከ1 ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

159. **ዓላማን በህገወጥ መንገድ ማስፋፋት የተከለከለ ስለመሆኑ**

1/ የአንድን የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማ በኃይል ወይም በማስፈራራት ለማስረጽ ማንኛውንም ሰው ወይም ቡድን ማደራጀት ወይም ማሰልጠን ወይም ሰዎችን በግድ መመልመል በህግ ያስቀጣል፡፡

2/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተገለፀውን ተግባር ሲፈጸም የረዳ ወይም የተባበረ ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

**ክፍል ዘጠኝ**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

160. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 100(ሀ) ያሉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ መሆን የሚጀምሩት የዚህን አዋጅ መጽደቅ ተከትሎ ከሚደረገው የፌደራልና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫን ቀጥሎ ካለው የበጀት አመት ጀምሮ ነው፡፡

2/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተመዘገበ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ የተቀመጡትን መስፈርቶች ቦርዱ በሚያስቀምጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እንዲያሟላ ይደረጋል፡፡

3/ ከላይ በንኡስ አንቀጽ ሁለት መሠረት የሚቀመጡትን መስፈርቶች ቦርዱ በሚሰጠው የጊዜ ሰሌዳ ያላሟላ ፓርቲ ቦርዱ ከምዝገባ እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል፡፡

161. **የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

162. **የተሻሩ ሕጎች**

1. የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡
   - ሀ/ የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 532/2007፣
   - ለ/ የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000፣
   - ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ ምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002፣

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

163. **መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

ቦርዱ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 164. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

--------/2011 ዓ.ም.

**ሳህለወርቅዘውዴ**
**የኢትዮጵያፌዴራላዊዴሞክራሲያዊሪፐብሊክፕሬዚዳንት**